# መጽሐፈ ኢያሱ

ትምህርት አንድ

## የመጽሐፈ ኢያሱ መግቢያ

ተርጓሚ፡ እሸቴ በለጠ

THIRD MILLENNIUM MINISTRIES
Biblical Education. For the World. For Free.

© 2017 by Third Millennium Ministries

All rights reserved. No part of this publication may be reproduced in any form or by any means for profit, except in brief quotations for the purposes of review, comment, or scholarship, without written permission from the publisher, Third Millennium Ministries, Inc., 316 Live Oaks Blvd, Casselberry, Florida 32707.

# እናስተዋውቅዎ

የሰርድ ሚሊኒየም ሚኒስትሪ እንደ አውሮፓውያኑ አቆጣጠር በ1997 ዓ.ም. ተመሠረተ፡፡ ይህ አገልግሎት አትራፊ ያልሆነ ድርጅት ሲሆን፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮዎችን ለመላው ዓለም በነጻ ለማዳረስ የተቋቋመ ነው፡፡ በዓለም አቀፍ ደረጃ ያለውን ጤናማ፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ - መሠረት ያለው ክርስቲያናዊ የአመራር ስልጠና ፍላጎት ምላሽ ለመስጠት፣ ምንም ዓይነት የስልጠና ግብዓቶች የማግኘት እድል ለሌላቸው ክርስቲያን መሪዎች የሴሚነሪ ሥርዓተ-ትምህርቶችን በማዘጋጀት እናሰራጫለን፡፡ ሰርድ ሚሊኒየም ሚኒስትሪ በመላውም ዓለም ለሚገኙ ክርስቲያን መሪዎችና ፓስተሮች የተመጣጠነ ዋጋ ያለው፣ በደጋፊዎች የሚታገዝ፣ ለተጠቃሚው ምቹ፣ በልዩ ልዩ የመገናኛ ብዙሃን ዘዴዎች የታገዘ ሥርዓተ-ትምህርት በአምስት ቋንቋዎች (በእንግሊዝኛ፣ በስፓኝ፣ በራሺያኛ፣ በማንዳሪን ቻይንኛ እና በአረብኛ) አስተርጎሞ አሰራጭቷል፡፡ ሁሉም ትምህርቶች የተጻፉት፣ የተዘጋጁት እና የታተሙት በአገልግሎቱ ውስጥ ሲሆን በ The History Channel©. ካሉት ጋር በቅርፅና በጥራት ተመሳሳይነት አላቸው፡፡ የሰርድ ሚሊኒየም ሥራ ማለትም ጥራት ላለው የማስተማሪያና የአኒሜሽን የቪዲዮ ፕሮዳክሽን ሥራዎቹ ሁለት የቴሊ አዋርድ ሽልማቶችን ተቀብሏል፡፡ የማስተማሪያ ግብዓቶቻችን በዲቪዲ፣ በህትመት፣ በኢንተርኔት ማስተላለፊያ ዘዴዎች፣ በሳተላይት የቴሌቪዥን ስርጭት፣ በራዲዮና በቴሌቪዥን ስርጭቶች ለማቅረብ በሚያስችል መልክ የተቀረፁ ናቸው፡፡ ሥርዓተ-ትምህርታችን በአሁኑ ወቅት ከ192 በላይ በሆኑ አገሮች ውስጥ አገልግሎት ላይ ውሏል፡፡

ስለ አገልግሎታችን የበለጠ መረጃ ለማግኘትና እንዴት የአገልግሎቱ ተጠቃሚ መሆን እንደምትችሉ ማወቅ ከፈለጋችሁ፣ www.thirdmill.org የተሰኘውን ድረ-ገጽ ጎብኙ፡፡

## ማውጫ


1. **መግቢያ**
2. **ጸሐፊና ወቅት**
    2.1. ትውፊታዊ አመለካከት
    2.2. ስህተት ነቃሽ አመለካከት
    2.3. የወንጌል አማኞች አመለካከት
        ሀ. እድገት
        ለ. አፈጻጸም

3. **ቅርጽና ዓላማ**
    3.1. ይዘትና አወቃቀር
        ሀ. በድል አድራጊነት መውረስ (1-12)
        ለ. የነገዶች ርስት ክፍፍል (13-22)
        ሐ. በቃል ኪዳን መታመን (23-24)
    3.2. ቀደምት ትርጓሜ
        ሀ. በድል አድራጊነት መውረስ
            1. ቅድመ ፍጥረተ-ዓለማዊ ጦርነት
            2. የእስራኤላውያን ልዩ ግጭት
            3. የእስራኤል ንጉሥ የወደፊት ድል
        ለ. የነገዶች ርስት ክፍፍል
            1. ጥንታዊ የሰው ዘር ገዢነት
            2. የእስራኤል ልዩ ውርስ
            3. የእስራኤል ንጉሥ የወደፊት ውርስ
        ሐ. በቃል ኪዳን መታመን
            1. ጥንታዊ የሰው ዘር ታማኝነት
            2. የእስራኤል ልዩ የቃል ኪዳን ታማኝነት
            3. ከእስራኤል ንጉሥ ጋር የሚኖረው የወደፊት ቃል ኪዳን

4. **ክርስቲያናዊ ተዛምዶ**
    4.1. አጀማመር
        ሀ. በድል አድራጊነት መውረስ
        ለ. የነገዶች ርስት ክፍፍል
        ሐ. በቃል ኪዳን መታመን
    4.2. እድገት
        ሀ. በድል አድራጊነት መውረስ
        ለ. የነገዶች ርስት ክፍፍል
        ሐ. በቃል ኪዳን መታመን
    4.3. ሙላት
        ሀ. በድል አድራጊነት መውረስ
        ለ. የነገዶች ርስት ክፍፍል
        ሐ. በቃል ኪዳን መታመን

5. **ማጠቃለያ**

# መግቢያ

በመላው ዓለም የሚኖሩ ህዝቦች አገሮቻቸው ሲመሠረቱ በነበሩት የታላላቅ ክንውኖች ክብረ በዓላት ታላቅ ፌሽታና ፈንጠዝያ ያደርጋሉ ያንንም ሲያስቡ እጅግ ደስተኞች ይሆናሉ፡፡ ሆኖም ውሎ ሲያድርና የወደፊቱ ትውልዶች ከተለያዩ ፈተናዎች ጋር ሲጋፈጡ፣ ክስረትና ተስፋ መቁረጥ ሲያጋጥማቸው፣ በቀደሙት ዓመታት የነበሩትን እነዚያን የድል ጊዜያት ማሳሰብና ምን ያህል ወሳኞችም እንደሆኑ ማስገንዘብ ይገባል፡፡ ይኸው ተተመሳሳይ ልምድ፣ በብዙ መንገዶች በብሉይ ኪዳኑ የኢያሱ መጽሐፍ ውስጥ ተንጸባርቆ ይገኛል፡፡ እስራኤላውያን ወደተስፋዪቱ ምድራቸው ለመጀመሪያ ጊዜ ሲገቡ እነዚህ የታላላቅ ድሎች ክብረ በዓላት በድምቀት ተከብረዋል፡፡ ሆኖም ቀጣዩ ትውልድ የተለያዩ ፈተናዎች ሲገጥሙት፣ እነዚያ የታላላቅ ድሎች ክብረ በዓላት ፋይዳ ምን ያህል ወሳኝ እንደሆነ መላልሶ ማሳሰብ እጅግ ወሳኝ ሆኗል፡፡

መጽሐፈ ኢያሱ ከተሰኘው ተከታታይ ትምህርታችን ይኸኛው የመጀመሪያው ትምህርት ሲሆን፣ "የመጽሐፈ ኢያሱ መግቢያ" የሚል ርእስ ሰጥተነዋል፡፡ መጽሐፈ ኢያሱ ለጥንታዊቷ እስራኤል ምን ትርጉም እንደሚሰጥ ስናስተውል፣ ዛሬ ለእኛ ዘመን ምን ያህል የከበረ ነገር እንደሚያስተላልፍልን ጥርት አድርገን ማየት እንድንችል ያግዘናል፡፡

የመጽሐፈ ኢያሱ መግቢያችን በሦስት ክፍሎች ይከፈላል፡፡ በመጀመሪያ፣ ጸሐፊውንና ወቅቱን እንመረምራለን፡፡ ሁለተኛ፣ ቅርጹንና ዓላማውን በወፍ በረር እናስተዋውቃለን፡፡ ሦስተኛ ደግሞ፣ በመጽሐፉ ላይ ተመሥርተን ክርስቲያናዊ ተዛምዶ በምንሠራበት ወቅት በልቡናችን ውስጥ ልናስቀምጣቸው የሚገቡንን የተለያዩ መጠነ ሰፊ አተያዮችን እንዳስሳለን፡፡ አስቀድመን በመጽሐፈ ኢያሱ ጸሐፊና ወቅት እንጀምር

# ጸሐፊና ዘመን

መጽሐፈ ኢያሱ በመንፈስ ቅዱስ መነዳት ተጽፏል በዚህም ምክንያት እውነተኛ ታሪካዊ መረጃን ያቀርብልናል ማለት ነው፡፡ ይህ ሲሆን ግን መንፈስ ቅዱስ ሰብዓዊ ሰዎች ታሪካዊ ሰነዶቻቸውን በሚያቀናብሩ ወቅት በቅዱሳት መጻሕፍት አመለካከትና ዓላማ መሠረት ጽሑፎቻቸውን ቅርጽ እንዲያስይዙ እንደተገለገለባቸው ማስታወስ ይገባል፡፡ እንግዲያው፣ ልክ እንደተቀሩት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ሁሉ፣ የሰብዓዊ ጸሐፊውን ማንነትና ዘመኑን ጠንቅቀን ከተረዳን፣ የኢያሱን መጽሐፍ በተሻለ መንገድ እንረዳለን ማለት ነው፡፡

የመጽሐፈ ኢያሱን ጸሐፊና ዘመኑን አስመልክቶ ሦስት መሠረታዊ አመለካከቶች በጥቂቱ እንዳስሳለን፡፡ በመጀመሪያ፣ ትውፊታዊ አመለካከቶችን፤ ሁለተኛ፣ ዘመናዊውን ስህተት ነቃሽ አመለካት፤ ሦስተኛ ደግሞ፣ ወደዚህ ትምህርት የሚመራንን ጥቂት መሠረታዊ የወንጌላውያን አመለካከቶችን ይሆናል፡፡ አስቀድመንም በመጽሐፉ ጸሐፊና በተጻፈበት ዘመን ረገድ ያለውን ጥንታዊ ትውፊታዊ አመለካከት እንመልከት፡፡

# ትውፊታዊ አመለካከቶች

መጽሐፈ ኢያሱ የጸሐፊው ስም በግልጽ ያልተጠቀሰበት መጽሐፍ ነው፡፡ መጽሐፉ ራሱ፣ ወይም የተቀሩት ቅዱሳት መጻሕፍት የመጽሐፉ አቀናባሪ ወይም ጸሐፊ ማን እንደሆነ አይነግሩንም፡፡ በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ "መጽሐፈ ኢያሱ" ተብሎ የተጠቀሰው ርዕስ፣ መጽሐፉ ከተጻፈ ከረዥም ጊዜ በኋላ የገባ ነው፡፡ ይህንን ጉዳይ አስመልክቶ ጥንታውያኑ አይሁድና ክርስቲያኖች የያዙት አቋም በታልሙድ ውስጥ በምናገኘውና የአይሁድን ራቢዎች አመለካከት በሚያንጸባርቀው በተከታታይ ጥያቄና መልሶች መልክ በቀረበው Tractate Baba Bathra 15, በመባል በሚታወቀው የታልሙድ ክፍል ጠቅለል ብሎ እንዲህ ተቀምጧል፡፡

> *ኢያሱ ራሱ መጽሐፉን ጽፏል (ትላላችሁ)፣ ግን "የጌታ ባሪያ የነዌ ልጅ ኢያሱ ሞተ" ተብሎ ተጽፎ የለምን? - የተጠቃለለው በአልዓዛር ነዋ፡፡ ግን ደግሞ "የአሮን ልጅ አልዓዛር ሞተ" ተብሎም ተጽፎ የለምን?- ፊንሐስ ነው የደመደመው፡፡*

በዚህ ስፍራ እንደምንመለከተው፣ የመጽሐፉን አብዛኛ ክፍል ራሱ ኢያሱ እንደጻፈው ተቀዳሚዎቹ የአይሁድ መምህራን (ራቢዎች) አመልክተዋል፡፡ ግን ደግሞ ጥቂቶቹ የመጽሐፈ ኢያሱ ክፍሎች ከኢያሱ መሞት በኋላ እንደተጻፉም እውቅና ሰጥተዋል፡፡ በ24፡9 ላይ የሚገኘውንና የኢያሱን ሞት ዘገባ ለሊቀካህኑ ለአልዓዛር ሰጥተዋል፡፡ በ24፡33 ላይ የሚገኘውን የአልዓዛርን ሞት ዘገባ ደግሞ፣ የአልዓዛር ልጅ ለሆነው ለፊንሐስ ሰጥተዋል፡፡ ከዚህ ትውፊታዊ አመለካከት በመነሳት መጽሐፈ ኢያሱ የተጻፈው በመጽሐፉ ውስጥ የተጠቀሱት ክንውኖች ከተከናወኑ በኋላ ብዙም ሳይቆይ እንደሆነ እንረዳለን፡፡

እንደ እውነቱ፣ የዚህን የታልሙድ አገላለጽ የሚያጸና ጥቂት ወይም ምንም ማስረጃ አልተገኘም፡፡ ሆኖም፣ በዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍ ጸሐፊነት ኢያሱ፣ አልዓዛርና ፊንሐስ የየበኩላቸውን ድርሻ ሊያበረክቱ አይችሉም ብለን ልንደመድምም አንችልም፡፡ ቀደም ብሎም በዘጸዓት 17፡14 ውስጥ፣ የእስራኤላውያንን ጥንታዊ የታሪክ መዛግብት ጠብቆ በማቆየት አደራ ውስጥ ኢያሱ ተሳታፊ እንደነበር እናውቃለን፡፡ በተጨማሪም፣ በኢያሱ 8፡32 እና 24፡26 እንደተጠቀሰው የእግዚአብሔር ህግጋት አጠቃቀም መመሪያ ሲጻፍም ኢያሱ ተቆጣጣሪ ነበር፡፡ ተመሳሳይ በሆነ መንገድም፣ አልዓዛርንና ልጁን ፊንሐስን የመሳሰሉ ካህናትና ሌዋውያን ቅዱሳት መጻሕፍትን በማስተማሩና በጥንቃቄ በመጠበቁ ረገድ ወሳኝ ሚና ነበራቸው፡፡

የመጽሐፈ ኢያሱ ጸሐፊ መጽሐፉን ሲያጠናቅር የተለያዩ የጽሑፍ ማስረጃዎችን እንደተጠቀመ፣ ከጥቂት ቆይታ በኋላ እንደርስበታለን፡፡ እናም ኢያሱ፣ አልዓዛርና ፊንሐስ ደግሞም እነርሱን የመሳሰሉ ብዙዎች፣ ቢያንስ ቢያንስ፣ በተዘዋዋሪ መንገድ ለእነዚህ ምንጮች የየራሳቸውን ድርሻ ሊያበረክቱ እንደሚችሉ ማሰብ ይቻላል፡፡

> *መጽሐፈ ኢያሱ ስለ አጻጻፉ ሁኔታ ፍንጭ ይሰጠናል፡፡ በምዕራፍ 18 ውስጥ ድርሻቸውን ስላልተረከቡ ስለ ሰባቱ ነገዶች፣ ወደ ኢያሱ እንደመጡና ስለ ጉዳዩ እንደጠየቁት እርሱም ከነገዶቹ ሰዎችን እንደመደበላቸው እና ወደ ምድሪቱ ሄደው በመመልከት ምድሪቱ ምን እንደምትመስል ዘገባ እንዲያቀርቡለት እንዳዘዛቸው ይዘግብልናል፡፡ ለእኔ እንደሚመስለኝ፣ ከምዕራፍ 18-20 የምናገኘው መግለጫ የሚያሳየን ለነገዶቹ ስለ ተደለደሉት ምድሮች ሲያወሩ፣ የከተሞቻቸውንና የግዛታቸውን ድንበሮች ማመልከታቸው እንደሆነ ነው፡፡ ስለዚህም፣ እነዚያ ሦስት ምዕራፎች ቢያንስ በቀዳሚነት የተጻፉት ምድሪቱን እንደገና ሄደው እንዲቃኙ ሃላፊነት በተሰጣቸውና ሪፖርቱን ከመግለጫ ጋር አጠናቅረው በተመለሱ ሰዎች እንደሆነ እናስተውላለን … ምዕራፍ 24 እንደሚነግረን ደግሞ ይህንን የርስት ክፍፍል ኢያሱ በህግ መጽሐፍ ያሰፈረው ሲሆን፣ በዚያን ወቅት ከእስራኤል ልጆች ጋር ያደረገውንም ቃል ኪዳን አካትቶ እንደጻፈ እናያለን፡፡ ያም የህግ መጽሐፍ ሙሴ ጽፎት የነበረው ሊሆን ይችላል፣ ይህም የሚሆንበት ምክንያት ኢያሱ በእግዚአብሔር ፊት አቆመው ስለሚል ነው፡፡ ጻፈው፤ በእግዚአብሔር ፊት አቆመው ይላል፡፡ በተመሳሳይ መንገድ ሙሴ የጻፈውም በእግዚአብሔር ፊት ማለትም በመገናኛው ድንኳን ውስጥ የተቀደሰ ቅርስ ሆኖ ተቀምጧል፡፡ እናም ስለዚህ፣ ይህ በኢያሱ በቀጥታ የተጻፈውም ክፍል በመጽሐፈ ኢያሱ ውስጥ በግልጽ ተቀምጧል ማለት ነው፡፡ በኢያሱ መጽሐፍ መጨረሻ ላይ የምናገኘው የርስት መግለጫና፣ የቃል ኪዳኑ ዘገባ እውነተኛ ከሆነ፣ ዝርዝር ዘገባዎችን ያካተቱት ስለ ውኂያዎቹ የተዘረዘሩትም መግለጫዎች ትክክለኛ ናቸው ማለት ሲሆን፣ ከነሙሉ ዓላማቸውና ግባቸው በቀደምትነት በኢያሱ ተጽፈዋል ማለት ነው፡፡* — *ዶ/ር ቺፐ ማክዳኒኤል*

የመጽሐፈ ኢያሱን ጸሐፊና የተጻፈበትን ዘመን አስመልክቶ የተመለከትናቸውን ትውፊታዊ አመለካከቶች በልቡናችን ይዘን፣ ዘመነኛውን ስህተት ነቃሽ አመለካከት ወደማየቱ እንሸጋገር፡፡ እነዚህ አመለካከቶች በአብዛኛው የሚቀነቀኑት የቅዱሳት መጻሕፍትን ባለሙሉ ሥልጣንነት በሚያጣጥሉ ምሁራን ነው፡፡

## ስህተት ነቃሽ አመለካከቶች

በኢያሱ መጽሐፍ ላይ አመለካከታቸውን ያሰፈሩት አብዛኞቹ ዘመናውያን ስህተት ነቃሽ ምሁራን በ1943 ዓ.ም. በተጻፈውና The Deuteronomistic History በተሰኘው የማርቲን ኖርዝ ሥራ ብርቱ ጫና አርፎባቸዋል፡፡ በአጭሩ ለማስቀመጥ፣ በኖርዝ አመለካከት፣ የዘዳግም፣ የኢያሱ፣ የመሳፍንት፣ የሳሙኤል እና የነገሥት መጻሕፍት የተጻፉት በባሎን ምርኮ ወቅት ሲሆን፣ የጻፋቸውም "ዘዳግማዊ" በመባል በሚታወቅ ሰው እንደሆነ ይታሰባል፡፡ በዚህም አመለካከት መሠረት፣ አጠቃላዩ የዘዳግም ዘመን ታሪክ፣ ማለትም የዛዳግምን መጽሐፍ ጨምሮ፣ የተጻፈው በባቢሎን ምርኮ ወቅት ከተሰባሰቡ ጥንታዊ ጽሑፎች ተጠረቃቅሞ ነው ይላሉ፡፡ የእነዚህ መጻሕፍት ዓላማም በሰሜናዊው እና በደቡባዊው መንግሥታት ላይ የወደቀው እና እስራኤልን ለሽንፈትና ለምርኮኛነት የዳረገው የእግዚአብሔር ፍርድ አግባብነት ያለው መሆኑን ለማሳየት ነው፡፡

ባለፉት ዐሥርት ዓመታት ውስጥ የነበሩ አብዛኞቹ፣ ስህተት ነቃሽ ተርጓሚዎች፣ የኖርዝን ማዕከላዊ አመለካከት፣ በተለይም የመጽሐፉ ጸሐፊ በባቢሎን ምርኮ ወቅት እንደነበረ የሚገልጸውን ይሁንታ ይሰጡታል፡፡ ይህም ሆኖ ግን፣ በርካታ ስህተት ነቃሽ ምሁራን በዚህ የብሉይ ኪዳን ኪዳን መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙትን ለየት ያሉ ነገረ-መለኮታዊ አመለካከቶች ኖርዝ ስቷቸዋል በማለት በትክክለኛው መንገድ ይሞግታሉ፡፡ በተጨማሪም ኖርዝ በእነዚህ መጻሕፍት ውስጥ የተጠቀሱትን አዎንታዊና ተስፋን ፈንጣቂ አመለካከቶችን ቸል ብሏቸዋል በማለት ሙግታቸውን ይሰነዝራሉ፡፡

በመጽሐፋችን ጸሐፊና በተጻፈበት ዘመን ላይ የተሰነዘሩትን ትውፊታዊና ስህተት ነቃሽ አመለካቶች ከዳሰስን፣ አሁን ደግሞ ጥቂት ዘመናዊ ወንጌል አማኝ አመለካከቶችን እንመልከት፡፡ እነዚህ አመለካከቶች የሚቀነቀኑት የቅዱሳት መጻሕፍትን ሥልጣን በሚያረጋግጡ ምሁራን ነው፡፡ እነዚህ አመለካከቶችም በዚህ ትምህርታችን የምንዳስሳቸውንና መጽሐፈ ኢያሱን ለመመልከት የምንሄድባቸውን መንገዶች አቅጣጫ የሚያስይዙልን ናቸው፡፡

## ወንጌል አማኝ አመለካከቶች

ቀደም ብለን እንደጠቀስነው፣ የመጽሐፈ ኢያሱ ጸሐፊ በግልጽ አልተጠቀሰም፡፡ በዚህም ምክንያት፣ ስለ ጸሐፊውና ስተጻፈበት ዘመን የተለያዩ አመለካከቶችን ያራምዳሉ፡፡ ይህም ሆኖ፣ ሁለት ምልከታዎችን ማድረግ በጣም ጠቃሚ ነው፡፡ በመጀመሪያ፣ እኛ የመጽሐፉ ጥንቅራዊ እድገት ብለን የምንጠራውን እንመለከታለን፡፡ ሁለተኛ ደግሞ፣ ጥንቅሩ የተጠናቀቀበትን የጊዜ ርዝማኔ ገደብ እንዳስሳለን፡፡ አስቀድመን የኢያሱን መጽሐፍ ጥንቅራዊ እድገት እንቃኝ፡፡

### እድገት

ስለ መጽሐፋችን እድገት ስናነሳ፣ በልቡናችን የያዝነው፣ ልክ እንደተቀሩት የብሉይ ኪዳን ጸሐፊዎች፣ የኢያሱም ጸሐፊ ታሪኩን ከመነሻው ጀምሮ ከራሱ ብቻ de novo ወይም ሌላ ምንም ምንጭ ሳይጠቀም ከዜሮ ጀምሮ አልጻፈውም የሚለውን ነው፡፡ ይልቁኑ፣ መጽሐፉን ሲያዘጋጅ የተለያዩ ጽሑፎችን በምንጭነት በመጠቀም አጠናቅሯል፡፡ እንደተመለከትነው፣ ታልሙድም ሆነ ስህተት ነቃሽ ተርጓሚዎች እንዳረጋገጡት መጽሐፋችን አንዳንድ ጥንቅራዊ እድገቶችን በውስጡ ይዟል፡፡ እናም፣ እንዲያውም በእጅጉ፣ ወንጌል አማኞችም ጸሐፊአችን ግብዓቶችን የመጠቀሙን ጉዳይ እውቅና ይሰጡታል፡፡

ይህም አበባል በ10፡13 ላይ ጸሐፊአችን ራሱ ሲጠቅስ መጽሐፍ ወይም የያሱር ጥቅልል ብሎ ከጠቀሰው በመነሳት በተወሰነ መጠን እውነትነት እንዳለው አስረግጠን እናውቃለን፡፡ ስለዚህ መጽሐፍ እኛ በእርግጠኝነት ባናውቅም፣ ጸሐፊአችንና ቀደምት ተደራሲያኑ በግልጽ ያውቁታል፡፡ ከዚህም ባሻገር፣ በዚህ ተከታታይ ትምህርታችን ደጋግመን እንደምናነሳው፣ ጸሐፊአችን ከፔንታቱክና ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጪ ካሉ ምንጮች አንዳንድ ሃሳቦችን እንዳካተተ እናያለን፡፡ የተጋነነ ግምት ካላስቀመጥን በስተቀር በግልጽ የማናውቃቸውን እነዚህን ምንጮች እንደገና ማዋቀር አንችልም፡፡ ሆኖም ጸሐፊአችን ጥንታዊ ምንጮችን፣ ማለትም የያሱር መጽሐፍ የተሰኙትን እንደተጠቀመ ማወቃችን መጽሐፉ ለምን ድግግሞሽ እንደበዛበት አንዳንድ ጊዜም የማይያያዝ ሊሆን እንደቻለ እንድንረዳ ያግዘናል፡፡

ይህ የጥንታዊ ምንጮች አጠቃቀም በተጨማሪ የሚያግዘን መጽሐፋችን የመጨረሻ ቅርፁን የያዘበትን ወቅት አስመልክቶ ከሚፈጠር ስህተት እንድንጠበቅ ነው፡፡ መጽሐፈ ኢያሱ በዐሥራ አምስት ቦታዎች ላይ፣ እነዚህም ጉዳዮች "እስከ ዛሬ ድረስ" እንደተጠበቁ ናቸው በማለት ይጠቅሳል፡፡ "እስከ ዛሬ ድረስ" የሚለው ሐረግ እስከ ጸሐፊው ዘመን ድረስ ለማለት እንደሆነ ማሰብ አዳጋች አይሆንም፡፡ ሆኖም፣ 1ኛ ነገሥት 8፡8 በመሳሰሉት ምንባቦች ላይ የተጠቀሰው "እስከ ዛሬ ድረስ" የሚለው ሐረግ ግን የሚያመለክተው እስከ ጥንታዊ ምንጮቹ ዘመን ድረስ ያለውን ነው፡፡

ምንም እንኳን መጽሐፈ ኢያሱ ጥንቅራዊ እድገት የሚታይበት መጽሐፍ መሆኑን ወንጌል አማኞች በጥቅሉ ቢስማሙበትም፣ ሆኖም ግን የመጽሐፉ ጥንቅር መቼ ተጠናቀቀ? የሚለው ጥያቄ ግን አሁንም በእንጥልጥል ያለ ጉዳይ ነው፡፡ አሁን በመጽሐፍ ቅዱሳችን በምናነበው መልክ ተቀናብሮ የተጠናቀቀው መቼ ነው?

#### አፈጻጸም

ልክ እንደተቀሩት በርካታ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ሁሉ፣ ጸሐፊአችን የኢያሱን መጽሐፍ መቼ እንዳጠናቀቀው በትክክል ማመልከት አንችልም፡፡ ማስረጃዎቹ የሚያግዙን ቀደም ባሉትና ዘግየት ባሉት ጊዜያት መካከል የሚገኙትን የጊዜ አማራጮች እንድንለይና ቀረቤታ ያላቸውን እንድናስተውል ብቻ ነው፡፡ ሆኖም በእነዚህ ትምህርቶቻችን እንደምንመለከተው፣ እነዚህን የጊዜ አማራጮች በልቡናችን ይዘን ስንመረምር፣ ጸሐፊአችን የቀደሙትን ተደራሲያኑን ለማሳመን መጽሐፉን እንዴት እንዳዋቀረው እንድንረዳ የሚያስችሉንን በርካታ ግንዛቤዎች እንጨብጣለን፡፡

መጽሐፈ ኢያሱ የተጠናቀቀበትን ዘመን አስመልክቶ የምንይዘውን ሰፋ ያለ የጊዜ አማራጭ በሁለት እርከኖች ከፍለን እንመለከተዋለን፡፡ በመጀመሪያ፣ ዘግየት ያለውን የጊዜ አማራጭ እንመረምራለን፡፡ ሁለተኛ ደግሞ፣ ቀደምትነት ያለውንና ሊሆን ይችላል ተብሎ የሚገመተውን ጊዜ እናያለን፡፡ አስቀድመን መጽሐፈ ኢያሱ ተጽፏል ተብሎ የሚገመትበትን ዘግየት ያለ ጊዜ በመመልከት እንጀምር፡፡

የኢያሱ መጽሐፍ ተጠናቅሮ የተጠናቀቀበትን የመጨረሻ ወቅት ከመለየት አንፃር ተመራጭ የሆነው መንገድ ከመጽሐፉ ውጪ ያሉትን ፍንጮች መመልከት ነው፡፡ የዘመናችን በርካታ ምሁራን የእስራኤል ቀደምት ታሪክ ብለው በሚጠሩት ስብስብ ውስጥ ጸሐፊአችን በዓላማ ያስገባቸው በርካታ መረጃዎች እንዳሉ ጥሩ ማስረጃ አለ፡፡ ይህም ታሪክ የሩት መጽሐፍን ሳይጨምር፣ ከዘፍጥረት አንስቶ እስከ ነገሥት መጽሐፍ ድረስ የሚዘልቀው ታሪክ ነው፡፡ ይህ አመለካከት እጅግ ወሳኝ ነው ምክንያቱም መጻሕፍቱ አንዳቸው ከሌላቸው ጋር የሚቀባበሉትና አንዳቸውን ከሌላቸው ጋር የሚያያይዛቸውን ቁልፍ የጊዜ መስመር ስለሚያመለክቱ ነው፡፡

እስኪ በዚህ መንገድ እንመልከተው፡ ፔንታቱክ የተሰኙት አምስቱ የሙሴ መጻሕፍት ከሙሴ ዘመን ጀምሮ ያሉትን የመጀመሪያ አምስት የዘመን እርከኖች አቀናብረው ያቀርቡልናል፡፡ ዘፍጥረት ከፍጥረት ይጀምርና ዮሴፍና ወንድሞቹን በግብጽ ምድር እያሳየን ይጠናቀቃል፡፡ ዘጸዓት ደግሞ ለዘፍጥረት ቀጥይነት እውቅና ይሰጣል ምክንያቱም አጀማመሩን ከዮሴፍ ሞትና ሐረግ ያረገውና አጨራረሱን ደግሞ ሙሴንና እስራኤላውያንን በሲና ተራራ ያደርገዋል፡፡ ዘሌዋውያን ደግሞ በሲና ተራራ ላይ የተከናወኑ ዝርዝር ጉዳዮችን ይተርክልናል፡፡ ዘኍልቁ ደግሞ እስራኤላውያን ከሲና ተራራ እስከ ሞዓብ ምድር ስላደረጉት ጉዞ ይዘግብልናል፡፡ ዘዳግም ደግሞ ሙሴ በሞዓብ ምድር ያደረጋቸውን ንግግሮችና የሙሴን ህልፈተ ሕይወት በመዘገብ አምስቱን መጻሕፍት ያጠናቅቅልናል፡፡

ተመሳሳይ በሆነ መንገድ፣ መጽሐፈ ኢሱ ደግሞ በቀደምት ታሪኩ ውስጥ የመጀመሪያ የሆነውን ዘዳግማዊ ሰንሰለት በግልጽ ያሳየናል፡፡ ይህም በዘዳግም መጽሐፍ ነገረ-መለኮታዊ አመለካከቶች ላይ በእጅጉ የሚደገፍና ያንኑ የሚያስገነዝብ ክፍል ያለበት ነው፡፡ የኢያሱ ጸሐፊ በሙሴ ሞት ይጀምርና በኢያሱ ሕልፈተ ህይወት ታሪኩን ወደ ቀጣይነት ያሸጋግረዋል፡፡ መሳፍንት ደግሞ የዘገባውን መነሻ በኢያሱ መጽሐፍ ማብቂያ ከሰፈረው የእስራኤል ታሪክ ያደርገዋል፡፡ መጽሐፈ ሳሙኤል ደግሞ የእስራኤል የመጨረሻ መስፍን በሆነው በሳሙኤል መነሳት ይጀምርና በዳዊት ንግሥና ይጠናቀቃል፡፡ የነገሥት መጽሐፍ ደግሞ የቀደምት ታሪኩን የመጨረሻ እርከን በማሳየት በዳዊት ሞት ይጀምርና በባቢሎን ምርኮ ይጠናቀቃል፡፡ በዚህ ረገድ፣ የነገሥት መጽሐፍ ከዘዳግማዊ የታሪክ ዘመን ቀደምት መጻሕፍት ዝርዝር ውስጥ ይወጣል ማለት ነው፡፡ ይህም ጭብጥ የኢያሱ መጽሐፍ ተጠናቅሮ ስላለቀበት ዘመን እጅግ ወሳኝ ፍንጭ ይሰጠናል ማለት ነው፡፡ ያም ማለት መጽሐፉ ከነገሥት መጽሐፍ መጻፍ በፊት መጠናቀቅ አለበት ማለት ነው፡፡

ይህ ምልከታ ጠቃሚ ነው ምክንያቱም የነገሥት መጽሐፍ መቼ እንደተጻፈ የምናውቅበት በርካታ መረጃ አለ፡፡ በ2ኛ ነገሥት 25፥27-30 ተመዝግቦ የምናገኘውና ሁነት የመጨረሻው ዘገባ ነው፡፡ በዚህ ስፍራ የዳዊት ንጉሣዊ ዝርያ የሆነው፣ ዮአኪን፣ በ561 ዓ.ዓ. በባቢሎን ከእስር እንደተፈታ ተጽፎ እናነባለን፡፡ በዚህ ምክንያት፣ የነገሥት መጽሐፍ ከዚህ ቀን በፊት እንዳልተጠናቀቀ በእርግጠኝነት እናውቃለን፡፡ ከዚህም በላይ፣ በ539 ዓ.ዓ. የተከናወነውንና እጅግ ወሳኝ የሆነውን የእስራኤልን ከግዞት ነፃ መውጣት መጽሐፈ ነገሥት አልዘገበውም፡፡ የነገሥትን መጽሐፍ ሲጽፍ ነፃነቱ ተገኝቶ ቢሆን ኖሮ የእስራኤልን ከግዞት ነፃ መውጣት ሳይዘግበው ያልፋል ብሎ ማሰብ ጨርሶ አይሞከርም፡፡ እንግዲያው፣ የእስራኤልን ቀደምት ታሪክ ቅደም ተከተል በልቡናችን ይዘን፣ መጽሐፈ ኢያሱ የተጠናቀቀበት እጅግ የዘገየው ጊዜ በባቢሎን ምርኮ ወቅት መሆኑን እንገምታለን፡፡

ይህንን የዘገየ ጊዜ ገደብ በልቡናችን ይዘን፣ በሌላ አቅጣጫ ደግሞ ነገሩን እንመልከት፡፡ ይህም የኢያሱ መጽሐፍ ሊጠናቀቅ የሚችልበት ቀደምት ጊዜ መቼ ሊሆን ይችላል? የሚለው ነው፡፡ የኢያሱ መጽሐፍ የመጨረሻውን ቅርፁን የያዘበትን ቀደም ያለ ጊዜ መመልከት ብዙም አያዳግትም፣ ያም በመሳፍንት ዘመን፣ ማለትም ከኢያሱ ሞት በኋላ በመጡት ትውልዶች ነው የሚሆነው፡፡ ጸሐፊው በመጽሐፉ ማብቂያ ላይ በ24፡31 ያሰፈረውን ልብ እንበል፡

*ኢያሱ ባለበት ዘመን ሁሉ፥ ከኢያሱም በኋላ በነበሩት ለእስራኤልም ያደረገውን የእግዚአብሔርን ሥራ ሁሉ ባወቁት በሽማግሌዎች ዘመን ሁሉ፥ እስራኤል እግዚአብሔርን አመለኩ። (ኢያሱ 24፡31)*

ይህ ምንባብ የሚያጣቅሰውን ልብ በሉ፣ "ከኢያሱም በኋላ በነበሩ ሽማግሌዎች"፡፡ ተያይዞም "እስራኤል እግዚአብሔርን አመለኩ" መቼ? "ለእስራኤልም ያደረገውን የእግዚአብሔርን ሥራ ባወቁት ዘመን" ይላል፡፡ ይህ የእስራኤልን መንፈሳዊ ሁኔታ አዎንታዊ ገጽታ ያመለከተ ዘገባ ስለ ጸሐፊአችን አንድ አነገር ያመለክተናል፡፡ ከኢያሱ ሞት በኋላ የመጣው ቀጣይ ትውልድ እግዚአብሔርን በታማኝት ማገልገል እንዳልቀጠለ አውቋል ወይም አስተውሏል ማለት ነው፡፡ ይህም እውነታ በመሳፍንት መጽሐፍ ውስጥ በጉልህ የተሰመረበት ጉዳይ ነው፡፡ ስለዚህ መጽሐፉችን ሊጠናቀቅ የሚችልበት ቀደም ያለው ጊዜ በእስራኤል መሳፍንት ዘመን ነው ማለት ነው፡፡

በኢያሱ መጽሐፍ ውስጥ ተጠቅሰው የምናገኛቸው አንዳንድ ክንውኖች የተከናወኑት በመሳፍንት ዘመን ሊሆን እንደሚችል ፍንጭ ይሰጡናል፡፡ ለምሳሌ፣ በኢያሱ 19፡47 የዳን ነገድ በስተሰሜን ወገን ድንበር አልፈው እንደሄዱ ተጠቅሷል፡፡ ይህ ክንውን የተካሄደው በመሳፍንት ዘመን እንደሆነ መሳፍንት 18፡27 -29 ያሳየናል፡፡ እንግዲያው፣ መጽሐፉ የተጠናቀቀበት ቀደምት ጊዜ ይህ ወቅትነበር ብሎ ማሰብ ሚዛናዊነት አለው፡፡

አሁን ደግሞ፣ ልንጠቅሰው የሚገባ ነገር በርካታ ተርጓሚዎች ወቅቱን በነገሥታት ዘመን ነው ብለው መከራከሪያ ማቅረባቸውን ነው፡፡ መጽሐፉ የተጠናቀቀበት ቀደምት ጊዜ ይህ ነው ብለው በርካታ ምክንያቶችን ያቀርባሉ፡፡ እናም ይህ ሊሆን አይችልም ብለን አንከራከርም፡፡ ለዚህ አመለካከት ተቀዳሚ ማስረጃ ሆኖ የሚቀርበው በኢያሱ 11፡21 የተጠቀሰው ሃሳብ ሲሆን፣ እንዲህ ይነበባል፡

*በዚያን ጊዜም ኢያሱ መጣ፥ ከተራራማውም አገር ከኬብሮንም ከዳቤርም ከአናብም ከእስራኤልም ተራራማ ሁሉ ከይሁዳም ተራራማ ሁሉ የዔናቅን ልጆች ገደለ፤ ኢያሱም ከከተሞቻቸው ጋር ፈጽሞ አጠፋቸው። (ኢያሱ 11፡21)*

በዚህ ስፍራ እንደምናየው፣ ጥቅሱ "ከይሁዳም ታራራማ ሁሉ" ወይም የደቡቡን መንግሥት፣ "ከእስራኤልም ተራራማ ሁሉ" ወይም የሰሜኑን መንግሥት በማለት ከፋፍሎ ያስቀምጠዋል፡፡

ይህ ይሁዳንና እስራኤልን ለይቶ የመጥቀሱ ነገር ለአንዳንዶች መጽሐፉችን በ930 ዓ.ዓ. ከተፈጸመው የእስራኤል መንግሥት መከፈል አስቀድሞ ሊጠናቀቅ አይችልም የሚል ሃሳብ እንዲይዙ አድርጓቸዋል፡፡ ይህንን ካልን በኋላ ግን፣ የብሉይ ኪዳን ጥንታዊ የግሪክ ትርጉም የሆነው ሰብዓ-ሊቃናት (ሰፕቱዋጀንት) ይህንን ልዩነት አላስቀመጠም፡፡ በተጨማሪም ምሁራኑ ትክክለኛውን አጻጻፍ የተከተለው የዕብራይስጡ ወይስ የግሪኩ በሚለወ ሃሳብ ላይ ስምምነት የላቸውም፡፡ እንግዲያው፣ ኢያሱ 11፡21 ክፍፍሉን እውቅና ሰጥቶታል ማለት ቢቻልም፣ እርግጠኛ መሆን ግን አይቻልም፡፡

እነዚህን ማስረጃዎች በአንድነት ስናስቀምጣቸው ታዲያ፣ መጽሐፈ ኢያሱ የተጠናቀቀበት ቀደምት ጊዜ ሊሆን የሚችለው በመሳፍንት ዘመን ውስጥ አንድ ወቅት ላይ ነው፡፡ ሆኖም ደግሞ እጅግ የዘገየው ወቅት ደግሞ በነገሥታት ዘመን ሊሆን የመቻሉም ነገር ከግምት ውስጥ ሊገባ ይችላል፡፡ እንዲያውም ወደባቢሎን ምርኮ ዘመን የሚርቀው በጣም የዘገየው ዘመንም ከግምት ውስጥ ከመግባት ሊርቅ አይችልም፡፡ ብዙም ሳንቆይ እንደምንመለከተው፣ ይህንን የተሚላ የዘመን ርዝማኔ ከግምት ውስጥ ማስገባታችን የኢያሱ መጽሐፍ አሁን በያዘው ቅርፁ ምላሽ የሚሰጣቸውን ጉዳዮች በሙላት ለመገንዘብ ይረዳናል፡፡

ሰለ መጽሐፈ ኢያሱ ጸሐፊና ዘመን ያወቅናቸውን ጉዳዮች በልቡናችን ይዘን፣ ወደ ሁለተኛው ወመግቢያችን ክፍል እንሸጋገራለን፡፡ ያም የመጽሐፉ ቅርፅና ዓላማ ነው፡፡ ጸሐፊአችን የኢያሱ ዘመን ዘገባውን ያወቀቀረው እንዴት ነው? በዚህ መንገድስ ቅርጽ የሰጠው ለምድን ነው?

# ቅርፅና ዓላማ

የኢያሱን መጽሐፍ የሚመስሉ መጽሐፍ ቅዱሳዊ የታሪክ መጻሕፍትን በምናጠናበት ወቅት ሁሉ፣ ተመሳሳይ የሆኑ ታሪካዊ ክንውኖች በበርካታ መንገዶች ሊነገሩና ሁሉም ምንም የስህተት ፍንጭ ሳይሰጧችሁ ሊነገሩ እንደሚችሉ ሁልጊዜ ማስታወስ ወሳኝነት አለው፡፡ ታሪካዊ ክንውኖችን የሚዘግብ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለ መጽሐፍ ታሪኩን የሚያቀናብረው እና የሚዘግበው አንድን ዓላማ ለማሳካት አልሞ ሲሆን ያንንም ዓላማውን ለማሳካትና ቀደምት ተደራሲያኑን ለመሞገት ሲል በተወሰኑ አመለካከቶች ላይ አጽንዖት ያደርጋል፡፡

ወደፊት በምንመለከታቸወ ትምህርቶቻችን እነዚህን ጉዳዮች በጥልቀት የምንመለከት ሲሆን፣ ለአሁኑ ግን የኢያሱን መጽሐፍ ቅርፅና ዓላማ በሁለት እርከኖች ዳሰስ እናድርግ፡፡ በመጀመሪያ፣ ከዳር እስከ ዳር ሚዘልቀውን ይዘትና አወቃቀሩን እናስተዋውቃለን፣ በትልቁም የመጽሐፉን ቅደም ተከተል እንመለከታለን፡፡ ሁለተኛ ደግሞ፣ በቀደምት ትርጉሙ ላይ ሃሳብ እንሰነዝራለን፣ ያም ጸሐፊአችን በቀደምት ተደራሲያኑ ላይ ሊያሳድር የሚፈልገውን በጎ ተፅዕኖ ማለት ነው፡፡ አስቀድመን የኢያሱን መጽሐፍ ይዘትና አወቃቀር እንመልከት፡፡

## አወቃቀርና ይዘት

መጽሐፈ ኢያሱ በተለያዩ የስነ-ጽሑፍ ዓይነቶች የተዋቀሩ ሃያ አራት ምእራፎች ያሉት መጽሐፍ ነው፡፡ ትረካዎች፣ ዘገባዎች፣ በተጨማሪም ከተለያዩ ምንጮች የተሰባሰቡ ሰዎች እና የቦታ ዝርዝሮችን በውስጡ እናገኛለን፡፡ በዚህም ምክንያት፣ ተርጓሚዎች የኢያሱን መጽሐፍ የአወቃቀር ዝርዝር በተለያየ መንገድ ሊያስቀምጡት ይችላሉ፡፡ ሰፋ ባለ መልኩ ግን አወቃቀሩና ይዘቱ እንዴት ተያይዞ ሊሄድ እንደሚችል መመልከት እምብዛም አዳጋች አይሆንም፡፡

> *የብሉይ ኪዳኑ ምኁራን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ መጻሕፍቶች በውስጣቸው የያዙዋቸውን የስነ-ጽሑፍ ዓይነቶች ለመለየት የሚጠቀሙባቸው የተለያዩ ዘዴዎች አሏቸው፣ ሆኖም ጠቅለል ባለ መልኩ፣ መጽሐፈ ኢያሱ በውስጡ ሦስት ዋና የስነ-ጽሑፍ ዓይነቶች ይገኙበታል፡፡ አንደኛው ትረካ ወይም ታሪክ ብለን የምንጠራው፣ ለምሳሌ ያህልም የኢያሪኮ ጦርነት፣ ብለን የምንጠራውና ተመሳሳይ የሆኑ ሁነቶችን ማለት ነው፡፡ በተጨማሪ ደግሞ፣ የተለያዩ መዘርዝሮችን ለምሳሌ፣ የተለያዩ ነገዶች ከእግዚአብሔር የተሰጣቸውና የወረሷቸው ስፍራዎች መልክዓ ምድራዊ ዝርዝር መግለጫዎችን፣ ከአንዱ ወደ አንዱ ከአንዱ ወደ አንዱ በማከታተል ይዘረዝራል፡፡ ከዚያም በመቀጠል ንግግሮች የሠፈሩበት ስፍራም አለ፡፡ እነዚያም ንግግሮች በተለያዩ ሰዎች ለአንድ የማኅበረሰብ ክፍል የተደረጉ ንግግሮችን ያካትታል፡፡ በዚህም መሠረት ነገሩን በአንክሮ ስንመለከተው እነዚህ ሦስት ትልልቅ ክፍፍሎች ከመጽሐፉ ሦስት ዋና አወቃቀሮች ጋር የተዛመዱ እንደሆነ ማለትም አንደኛው ከመጀመሪያው ክፍል ጋር ሁለተኛው ከሁለተኛው ጋር እና ሦስተኛው ከሦስተኛው ጋር የሚዛመዱ ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡ የመጀመሪያው በተቀዳሚነት ትረካ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ በተቀዳሚነት መልክዓ ምድራዊ ዝርዝር ይሆናል፣ ሦስተኛው ደግሞ በተቀዳሚነት ንግግሮች ይሆናሉ ማለት ነው፡፡ ሆኖም ግን ይህን ስናደርግ ከአንድ ችግር ጋር ልንጋፈጥ እንደምንችል ማሰብ ይገባናል፣ ይህም ማለት፣ የመጽሐፉን ክፍልፋዮች በእነዚህ ሦስት ዋና የስነ-ጽሑፍ ጥላዎች ስር ስናካትታቸው አንዱን እያነበብን እያለ የተቀሩት ሁለቱ በመሃከል ብቅ ሊሉ ይችላሉ፡፡ ስለዚህ ንባባችንን በምናደርግበት ወቅት የቱ ጋ የቱ ዓይነት እንደገባ ለማስተዋል ንቁ መሆን ያስፈልገናል፡፡ በዚህ ረገድ ከሚያጋጥሙ ግራ መጋባቶች ወስጥ ዋነኛው ተርጓሚዎችን በተለይም አዳዲስ ተርጓሚዎችን ወይም ተማሪዎችን የሚያጋጥማቸው ግርታ ሲሆን፣ ይህም ግርታ የስነ-ጽሑፍ ዓይነቶቹን አለመለየትና እያንዳንዳቸውን የሚታዩበት የየራሳቸው ባህርይ እንዳላቸው አለመገንዘብ ነው፡፡ ስለዚህ ልክ እንደማገኘውም አንባቢ መጽሐፈ ኢያሱን ስናብብ፣ እነዚህን የተለያዩ የስነ-ጽሑፍ ዓይነቶች ካላስተዋልንና በመጽሐፉ ውስጥ እንዴት ተሰበጣጥረው እንደተቀመጡ ካልተረዳን፣ ወደ ትልቅ ግራ መጋባት ውስጥ ልንገባ እንችላለን፡፡*
>
> *ዶ/ር ሪቻርድ ኤል. ፕራት፣ ጁኒየር*

በአጭሩ፣ ኢያሱ ሦስት ዋና ክፍሎች አሉት፡፡ እያንዳንዱ ክፍል የዘመን ለውጥን የሚጠቁም ዐረፍተ ነገር በማስፈር ይጀምራል፡፡ የመጀመሪያው ክፍል፣ ምዕራፍ 1-12 ሲሆን፣ ትኩረት የሚያደርገው እስራኤል ከነዓንን ድል በማድረጓ ላይ ሲሆን፣ ያም እስራኤላውያን በከነዓናውያን ላይ ወሳኝ ድሎችን እንዲቀዳጁ ኢያሱ እንዴት እንደመራቸው የተዘገበበት ማለት ነው፡፡ ይህ ክፍል የሚጀምረው በ 1፡1 ውስጥ "ከሙሴ ሞት በኋላ" እግዚአብሔር ኢያሱን እንደላከው በመዘገብ ነው፡፡

## በድል አድራጊን መውረስ (1-12)

እነዚህ ዐሥራ ሁለት ምዕራፎች ኢያሱ ምድሪቱን በድል አድራጊነት በወረሰበት ዘመን የተከናወኑ በርካታ ድርጊቶችን በዝርዝር ይዘግባሉ፡፡ የሚጀምሩትም እስራኤላውያን ዮርዳኖስን መሻገራቸውንና በኢያሪኮና በጋይ ላይ ድል መቀዳጀታቸውን በመዘገብ ነው፡፡ እነዚህም ድሎች በገሪዛም እና በኤባል ተራሮች አካባቢ የተካሄዱ የቃል ኪዳን ተሃድሶ ስርዓቶችን አስከትለው ነበር፡፡ ትረካውም በመቀጠል በተስፋዪቱ ምድር ደቡባዊ ግዛቶች በሚገኙ ኃይሎች ላይ የተደረገውን የኢያሱ ዐቢይ ዘመቻ ወደ መዘገቡ ይሸጋገራል፡፡ ከዚያም ዘገባው በሰሜናዊ ግዛቶች በሚገኙ ኃይሎች ላይ የተሰነዘረውን ዘመቻ ያስከትላል፡፡

## የነገዶች ርስት ክፍፍል (13-22)

በምዕራፍ 13-22 የሚገኘው፣ የመጽሐፋችን ሁለተኛ ክፍል፣ ስለ እስራኤል ነገዶች የርስት ክፍፍል ያሳየናል፡፡ በዚያም ውስጥ ለእያንዳንዱ ነገድ እንደ ማንነቱ የሚገባውን የርስት ክፍፍል በማድረግ የእስራኤል ብሔራዊ አንድነት እንዴት ተጠብቆ እንዲቆይ እንደተደረገ እናስተውላለን፡፡ ይህ ክፍል ሚጀምረው በምዕራፍ 13፡1 በሚገኘው አጭር ዐረፍተ ነገር ማለትም፣ “ኢያሱም ሸመገለ በዕድሜም አረጀ” በሚለው ነው፡፡

የኢያሱ መጽሐፍ ሁለተኛው ዋና ክፍል እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን የሰጣቸውን ርስት ድንበር ያመለክታል፡፡ ይህም ድንበር ከዮርዳኖስ ማዶ ያሉትን ማለትም ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተምሥራቅ የሚገኙትን መሬቶች እና ከዮርዳኖስ መለስ ያሉትን ማለትም ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተ ምዕራብ ያሉትን መሬቶች ያካተተ ነው፡፡ በመቀጠልም ከዮርዳስ ማዶ ባሉት መሬቶች ውስጥ እንዲቀመጡ ስለተፈቀደላቸው የእስራኤል ነገዶች ማብራሪያ ይሰጣል፡፡ በማስከተልም ከዮርዳኖስ በስተ ምዕራብ በሚገኙት መሬቶች ውስጥ ለይሁዳ፣ ለኤፍሬምና ለምናሴ፣ ትልልቅ ርስቶችን እግዚአብሔር እንዴት እንደሰጣቸውና ለተቀሩት የስራኤል ነገዶች ደግሞ መጠነኛ ርስቶችን እንዴት እንደሰጣቸው ያትታል፡፡ ደግሞም ከዮርዳኖስ መለስና ከዮርዳኖስ ማዶ በሰፈሩ ነገዶች መካከል ግጭት በሚቀሰቀስበት ጊዜ እንኳን፣ እንደ እግዚአብሔር ህዝብ እንዴት አንድነታቸውን ጠብቀው እንዳቆዩ በግልጽ እንገነዘባለን፡፡

## በቃል ኪዳን መታመን (23-24)

በምዕራፍ 23 እና 24 ውስጥ የሚገኘው ሦስተኛው ዋና ክፍል፣ በእስራኤል የቃል ኪዳን መታመን ላይ ትኩረት በማድረግ መጽሐፋችንን መደምደሚያ ያደርግለታል፡፡ በዚያም ውስጥ ለእግዚአብሐር ቃል ኪዳን የእስራኤል መታመንም ሆነ አለመታመን እንዴት አድርጉ የወደፊቱን እጣ ፈንታ እንደሚወስነው ያሳየናል፡፡ የሚጀመምረውም በ23፡1 ላይ በሚገኘውና የዘመንን ማብቂያ በሚያመለክተው ዐረፍተ ነገር ነው፡፡ እንዲህ ይነበባል፣ “ብዙ ዘመን ከሆነ በኋላ፥ ኢያሱም በሸመገለ በዕድሜውም ባረጀ ጊዜ፥”፡፡ ይህም ዐረፍተ ነገር ተጠናክሮና ግልጽ ሆኖ የምናገኘው በቁጥር 14 ላይ “እነሆም፥ ዛሬ የምድርን ሁሉ መንገድ እሄዳለሁ፤” በማለት ኢያሱ በተናገራቸው ቃላት ነው፡፡

የመጽሐፋችን የመጨረሻዎቹ ሁለት ምዕራፎች የሚያተኩሩት ኢያሱ በመሞቻው አካባቢ በሰበሰባቸው ሁለት ጉባዔዎች ላይ ነው፡፡ ከእነዚህ የመጀመሪያው ጉባዔ የተካሄደው በኢያሱ ዘመን፣ ኋላም በመሳፍንት ዘመን ከፍተኛ አስተዋፅዖ በነበረው የተቀደሰ ስፍራ አሴሎ ሳይሆን አይቀርም፡፡ የሚደመደመው ደግሞ በሴኬም፣ ማለትም አብርሃም በከነዓን ምድር ውስጥ መሠዊን በሰራበት ምድር ውስጥ በተካሄደው ጉባዔ ነው፡፡ በእነዚህ ጉባዔዎች መላው እስራኤል የተሰበሰበ ሲሆን፣ የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን በግልጽ ስለመተላለፋቸው ኢያሱ ማሳሰቢያ ሰጥቷል፡፡ የመጽሐፋችን ዋነኛ አካል የሆነው ክፍል የሚደመደመው እራኤላውያን ለእግዚአብሔር ብቻ ታማኝ ሆነው መዝለቅ እንዳለባቸው ኢያሱ በሰጠው የተሃድሶ መልእክትና ምሪት ነው፡፡ ሌሎችን የአህዛብ አማልክት ከደው የአባቶቻቸውን አምላክ ከእነርሱ ጋር በገባው ቃል ኪዳን መሠረት ሊያመልኩ ቃል ኪዳን ገብተዋል፡፡ ይህንን የቃል ኪዳን ተሃድሶ ካሰፈረ በኋላ፣ መጽሐፉ የኢያሱን መሞትና ሌሎች በርካታ ክንውኖችን በመዘገብ ይጠቃለላል፡፡

የመጽሐፉን ይዘትና አወቃቀር በመቃኘት የኢሱን ንድፍና ዓላማ ስንመለከት ቆይተናል፡፡ አሁን ደግሞ የመጽሐፈ ኢያሱን ቀደምት ትርጓሜ እንዴት ማስቀመጥ ይገባናል? በሚለው ጥያቄ ላይ ወደ ምንነጋገርበት እርከን እንሸጋገራለን፡፡

# ቀደምት ትርጓሜ

በበርካታ መንገዶች፣ የኢያሱ መጽሐፍ ጸሐፊ ከተቀሩት የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎች ጋር የሚጋራው የተጻፈበት ዓላማ አለው፡፡ መጽሐፉን የነደፈው እግዚአብሔርን ለማክበር ነው፡፡ የእግዚአብሔርን የቃል ኪዳን መርሆች ከቀደምት ተደራሲኑ አስተሳሰቦች፣ ባህርያትና ስሜት ጋር በማዛመድ የእግዚአብሔርን መንግሥት የማስፋፋት ናፍቆት አለው፡፡ ሆኖም የኢያሱን መጽሐፍ በምናጠናበት ወቅት፣ ጸሐፊያችን መጽሐፉን በሚጽፍበት ወቅት ለየት ያለ ትኩረት ያደረገባቸውን ጉዳዮችም እናስተውላለን፡፡

የኢያሱን መጽሐፍ ቀደምት ትርጓሜ ጠቅለል አድርጎ ማቅረብ የሚቻልባቸው በርካታ መንገዶች አሉ፣ ሆኖም ግን ከእኛ ዓላማ አንጻር ከታች በሚገኙት መስመሮች ጠቅለል አድርገን እናስቀምጠዋለን፡

> ***የኢያሱ መጽሐፍ የተጻፈው በኢያሱ ዘመን ስለተከናወኑት ስለ ስራኤል በድል አድራጊነት መውረስ፣ ስለ ነገዶች የርስት ክፍፍልና በቃል ኪዳን መታመን ሲሆን በዚያም ቀጣይ ትውልዶች የሚገጥማቸውን ተመሳሳይ ተግዳሮት በአንክሮ ለማሳሰብም ጭምር ነው፡፡***

እንደምንመለከተው፣ ይህ ማጠቃለያ የኢያሱን መጽሐፍ ሦስት ዋና ክፍልፋዮች ያሳየናል፡፡ በድል አድራጊነት መውረስ፣ የነገዶች ርስት ክፍፍል እና በቃል ኪዳን መታመን ናቸው፡፡ ግን ጸሐፊችን በእነዚህ ጉዳዮች ላይ ለምን ትኩረት ማድረግ ፈለገ? ማጠቃለያችን እንደሚሳየን፣ በመጀመሪያ፣ በኢያሱ ዘመን ምን ምን ክንውኖች እንደነበሩ ተደራሲኑን ማሳሰብ ነው፡፡ ሁለተኛ ደግሞ፣ መጪው ትውልድም ተመሳሳይ ተግዳሮቶች እንደሚያጋጥሙት ማስገንዘብ ነው፡፡ በመጀመሪያ ጸሐፊው ለምን ስለ ኢያሱ ዘመን እንደጻፈ በመመልከት ሁለቱንም ዓላማዎች እንመልከታቸው፡፡

ስለ ኢያሱ መጽሐፍ እውቀት ያለው ሰው ሁሉ በቀላሉ እንደሚረዳው መጽሐፉ በቀጥታ የሚያወሳው ኢያሱ እስራኤልን ሲመራ በነበረበት ዘመን ስለተከናወኑ ድርጊቶች ነው፡፡ ይህም፣ እስራኤል የከነዓንን ምድር በድል አድራጊነት መውረሷን፣ ኢያሱ ለእስራኤላውያን በየነገዳቸው ርስትን ማከፋፈሉን እና እስራኤል ከእግዚአብሔር ጋር ለነበራት ቃል ኪዳን ነበራትን መታመን ያካትታል፡፡ ስለዚህ፣ ከጸሐፊአችን ማዕከላዊ ዓላማዎች አንዱ ቀደምት ተደራሲያኑ በዚያን በኢያሱ ዘመን በዓለም ላይ ምን እንደተከናወነ ለማሳወቅ ነው ብንል አግባብነት ይኖረዋል፡፡ በርካታ የብሉይ ኪዳን ምንባቦች ጫን ብለው እንደሚያሳዩን እስራኤላውያን እግዚአብሔር በቀደሙት ዘመናት ያደረገላቸውን ከመርሳታቸው የተነሳ ደግመው ደጋግመው መንገዱን ይስቱ ነበር፡፡ ጸሐፊአችንም በ 24፡31 ላይ *ለእስራኤልም ያደረገውን የእግዚአብሔርን ሥራ ሁሉ ባወቁት በሽማግሌዎች ዘመን ሁሉ፥* የምትለውን ሃሳብ በማስቀመጥ እርሱና ቀደምት ተደራሲያኑ ከላይ ከተጠቀሱት የተለዩ እንደሆኑ በማሳየት ችግሩ በቀደምት ተደራሲያኑ ውስጥ እንደነበር ፍንጭ ይሰጠናል፡፡

የመጽሐፉችን ቀደምት ተደራሲያን፣ በመሳፍንት ዘመንም ቢኖሩ፣ አሊያም በነገሥታቱ ዘመን ወይም በባቢሎን ምርኮ ዘመን ቢኖሩም፣ በኢያሱ ዘመን ምን ምን እንደተከናወነ ሊያውቁ ይገባቸው ነበር፡፡ ስለዚህ፣ በመሠረታዊ ደረጃ፣ የኢያሱ መጽሐፍ ጸሐፊ በኢያሱ ዘመን ስለተከናወኑት ነገሮች ቀደምት ተደራሲኑ እውነተኛ ዘገባ እንዲያገኙ የማድረግ ዓላማ ነበረው ማለት እንችላለን፡፡

በሁለተኛ ደረጃ፣ ማጠቃለያችን እንደሚያሳየን፣ የኢያሱ መጽሐፍ የተጻፈው ቀጣዩ ትውልድ የሚጠብቀውን ተግዳሮት ማሳየትን ዓላማ አድርጎ ተጽፏል፡፡ ጸሐፊአችን ልክ በሁለት ዓለማት መካከል እንደቆመ ይመስላል፡፡ ያም፣ "የቀደመው ዓለም" ማለትም በኢያሱ ዘመን የነበረው ዓለም እና "የእነርሱ ዓለም" ማለትም የቀደሙት ተደራሲያን የነበሩበት ዓለም ማለት ነው፡፡ በዚህም ምክንያት፣ ጸሐፊአችን እውነተኛ ታሪካዊ ጭብጦችን ዘግቦ ለማቆት ብቻ አልጻፈም ማለት ነው፡፡ ስለ እስራኤል በድል አድራጊነት መውረስ፣ ስለ ነገዶች የርስት ክፍፍል እና በቃል ኪዳን የመታመን ጥሪን ስለማቅረብ ሲዘግብ፣ "በቀደመው ዓለም" እና "የእነርሱ ዓለም" በሚላቸው ዓለሞች መካከል ያለውን ትርጉም የሚሰጥ ትስስር ለማሳየትም ጭምር ጽፏል ማለት ነው፡፡ ልክ እንደ ተቀሩት የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎች ሁሉ፣ ደግሞ ደጋግሞ ታሪካዊ ዳራዎችን የሚያመለክት ሲሆን ያም የእርሱ ተደራሲያን ያገኙትን እድልና ሃላፊነቶች የሚያብራሩ ናቸው፡፡ ሊቀበሏቸውና ላይቀበሏው የሚችሏቸውን ተምሳሊቶችም ያቀርብላቸዋል፡፡ በጥቂት ስፍራዎችም፣ በኢያሱ ዘመን የተከናወኑ ድርጊቶች የቀደሙት ተደራሲኑ ልምምዶች ጥላዎች እንደሆኑ በማሳየት ጽፏል፡፡

እነዚህን የመሳሰሉት ግንኙነቶች ጸሐፊአችንን አስመልክቶ በልቡናችን ልናስቀምጠው የሚገባንን አንድ ነገር ይገልጡልናል፡፡ በአንድ በኩል፣ ተደራሲያኑ በኢያሱ ዘመን ምን እንደተከናወነ እንዲያስታውሱ ይፈልጋል፡፡ በሌላ በኩል ግን፣ እስራኤላውያን በኢያሱ ዘመን የተደረጉ ነገሮችን ደግመው እንዲያደርጉ እንደማይፈልግም ያሳያል፡፡ የእርሱ ቀደምት ተደራሲያን የሚኖሩት በተለየ መን ነው፡፡ ስለዚህም የእርሱን ታሪካዊ ዘገባ ዛሬ ከሚኖሩበት ዘመን ጋር በማጣጣም በሕይወታቸው ተግባራዊ እንዲያደርጉ ይገባል፡፡

> ***የመጽሐፈ ኢያሱ ቀደምት ተደራሲያን በመልእክቱ በእጅጉ እንደተነኩ አምናለሁ፡፡ እግዚአብሔር የሰጣቸው ተስፋዎች፣ አንዳቸውም እንኳን ሳይቀሩ ወደ ተስፋዪቱ ምድር በመጡበት ወቅት ለእስራኤላውያን ተፈጽመው እንደነበሩ ያስተውላሉ፡፡ ሳይሳካ የቀረ አንድ እንኳን አልነበረም፡፡ እኔ እንደማስበውም፣ በዋናነት፣ እግዚአብሔር ታማኝ እንደሆነ፤ ታማኝ እንደነበረ እና ታማኝ ሆኖ እንደሚዘልቅ ህዝቡን ለማስተማር ነበር፡፡ በተለይም እነዚያ ሰዎች ወደ መሳፍንት ዘመን ሲሸጋገሩ ጉዳዩ በጣም ወሳኝነት ነበረው፡፡ ምክንያቱም በመሳፍንት ዘመን በግልጽ እንደምናየው እነርሱ የተገለጡበት መገለጫ በዐይናቸው ፊት መልካም መስሎ የታያቸውን የሚያደርጉ ሰዎች ተብለው ነበር፡፡ እነርሱ ተጠርተው የነበሩት ግን ለያህዌ ታማኝ ሆነው እንዲዘልቁ ነበር፡፡ በዚህም ምክንያት፣ መልእክቱ በኢያሱ እና ከኢያሱ ጋር በታማኝነት ጸንተው በነበሩ ሰዎች ሕይወት ውስጥ ይገለጥ የነበረውን ታማኝነት እና ዛሬ እነርሱ እየኖሩ ካሉበት ጋር በማስተያየት፣ የአሁኑ ትውልድ የኢያሱን ፈለግ በእውነት ተከትሎ እየተራመደ እንዳልሆነ እንዲያስተውሉ ማድረግ ነው፡፡ እናም ጥሪው በእውነት ንስሓ እንዲገቡ፣ ወደ ተጠሩበት ጥሪም እንዲመለሱ የማድረግ ጥሪ ነበር፡፡***

**ዶ/ር ቲ.ጄ. ቤትስ**

እንግዲህ በእኛ ዘመን በተደጋጋሚ፣ ይህንን ታሪካዊ ዘገባ ቀደምት ተደራሲኑ ከሕይወታቸው ጋር ሊያዛምዱት እንደሚገባ ከማስተዋል አንጻር ተርጓሚዎቻችን ዋናውን ጭብጥ ለማግኘት ሲቸገሩ እናስተውላለን፡፡ በመሠረቱ፣ ጸሐፊአችን እነዚህን ጉዳዮች ቃል በቃል አልጠቀሳቸውም፡፡ ሆኖም ጸሐፊችንና ተደራሲያኑ በእነርሱ ዘመን ከነበሩት ቅዱሳት መጻሕፍት ማለትም እኛ አምስቱ የሙሴ መጻሕፍት (ፔንታቱክ) ብለን ከምንጠራቸው እውቀትን ሊገበዩ እንደሚችሉ ማሰብ ይገባናል፡፡ ይህንን እሳቤ በልቡናችን አድርገን፣ ጸሐፊአችን “የቀደመው ዓለም” እና “የእነርሱ ዓለም” በማለት ያሰፈረው ዘገባ ለመጀመሪ ጊዜ ስናየው አንድምታው ምን እንደሆነ መለየት አያዳግተንም፡፡

## በድል አድራጊነት መውረስ

አምስቱ የሙሴ መጻሕፍት የእስራኤላውያንን በድል አድራጊነት የመውረስ አንድምታ ከመረዳት አንፃር ለቀደምት ተደራሲያኑ እንዴት መደላድል እንደሚሠራ እንመለከታለን፡፡ የመጽሐፋችን ይህኛው ክፍል ኢያሱ የተቀዳጃቸውን ድሎች ይዘግብልናል፡፡ ነገር ግን ከፔንታቱክ መጽሐፍ የተወሰዱት ሦስት መሠረታዊ የውጊያ አመለካከቶች፣ የኢያሱን ይህኛውን ክፍል እንዴት እንደሚዛምዱት ያሳያቸዋል፡፡

**ቅድመ ፍጥረተ-ዓለም ግጭት** - በመጀመሪያ ደረጃ፣ ጸሐፊአችንና የእርሱ ቀደምት ተደራሲያን በእግዚአብሔርና በሰይጣን መካከል በተደረገው ውጊያ ውስጥ እንደገቡ ያውቃሉ፡፡ የሰው ዘር በኃጢአት ከወደቀበት ጊዜ አንስቶ፣ በሰው ዘር ታሪክ ውስጥ በእግዚአብሔርና በሰይጣን መካከል ብርቱ ውጊያ እየተካሄደ መሆኑን ዘፍጥረት 3፡15 ያመለክተናል፡፡ ይህ ስውር ጦርነት በእባቡ ዘር ወይም ዝርያ መካከል ማለትም የሰይጣን ኃይላትን በሚያገለግሉ ሰዎች መካከልና በሴቲቱ ዘር ወይም ዝርያ ማለትም እግዚአብሔርን በሚያገለግሉ ህዝብ መካከል በሚደረግ ውጊያ በምድር ላይ በግልፅ ይታያል፡፡ የኢያሱ መጽሐፍ የእስራኤል ጦርነት ገሃድ ዓለማዊ ጦርነት ብቻ እንደሆነ አድርጎ ሊያሳንሰው ያልቻለው በዚህ ምክንያት ነው፡፡ ይልቁኑ፣ በኢያሱ 5፡14፣ ጸሐፊአችን “የእግዚአብሔር ሠራዊት አለቃ” በማለት መልአኩን ይጠቅስልናል፡፡ ይህ ምንባብ ኢያሱና የእስራኤል ሠራዊት እግዚአብሔርና የመላእክቱ ሰራዊት በተሳተፉበት ውጊያ ላይ እንደነበሩ ያሳየናል፡፡ ደግሞም፣ እንደ ኢያሱ 23፡16 የመሳሰሉት ምንባቦች፣ የከነዓናውያን ሰይጣናዊ አማልክት ደግሞ የእስራኤላውያን ጠላቶች ሆነው ከተሰለፉት ከከነዓናውያን ሠራዊት ጎን ቆመው እንደነበር ጸሐፊው እንደተረዳ ያመለክቱናል፡፡ የኢያሱ ቀደምት ተደራሲያን ከእስራኤል በድል አድራጊነት የመውረስ ታሪክ ብዙ የሚማሩት አለ፣ ልክ በኢያሱ ዘመን እንደነበሩት እስራኤላውያን ሁሉ፣

እነርሱም በእግዚአብሔርና በሰይጣን እርሱንም በሚገለግሉት መካከል ያለማቋጥ በሚካሄደው ውጊያ ውስጥ ተሳታፊ እንደሆኑ ስለሚያውቁ ነው፡፡

**የእስራኤላውያን ለየት ያለ ውጊያ፡፡** በሁለተኛ ደረጃ፣ የኢያሱ የእስራኤል ለየት ያለ ውጊያ እንደሆነ፣ ፔንታቱክ ግልጽ አድርጎ ያስቀምጥልናል፡፡ የቀደሙት ተደራሲያን ከእስራኤል ድል በርካታ ነገሮችን የሚማሩ ቢሆንም፣ እነርሱና ከእነርሱ ቀጥሎ የሚመጣው ትውልድ፣ እያንዳንዱን ዝርዝር ጉዳይ በቀጥታ ቀድተው ይተገብሩታል ማለት አይደለም፡፡ የኢያሱ ዘመን ከተለመደው እጅግ የተለየ ልዩ ዘመን እንደነበረ ፔንታቱክ በግልጽ ያስቀምጣል፡፡

በዘፍጥረት 15፡13-16 ውስጥ፣ "የአሞራውያን ኃጢአት" አሞራውያን የከነዓናውያን ሌላኛው መጠሪያ ነው፣ "ጽዋው ገና አልሞላምና" ዘርህ በግብጽ ምድር ለጥቂት ጊዜ ባሪያዎች ይሆናሉ በማለት እግዚአብሔር ለአብርሃም ነግሮታል፡፡ ነገር ግን፣ ኢያሱ ድል ባደረገበት ዘመን፣ የከነዓናውያን ኃጢአት እጅግ ከመብዛቱ የተነሳ፣ ልክ በአብርሃም ዘመን በሰዶምና በገሞራ ላይ ጥፋትን እንዳመጣ ዓይነት፣ እነርሱንም ፈጽሞ ሊያጠፋቸው እንደወሰነ እንረዳለን፡፡

ጸሐፊአችን የከነዓናውያንን ጥፋት ሲዘግብ ከፔንታቱክ ቃላት በመዋስ በዕብራይስጡ *ቻራም* የተባለውን ግስና *ቼሬም* የተሰኘውን ስም የተጠቀመው በዚህ ምክንያት ነው፡፡ ኢያሱ 6፡17፤ 19-21 እንደሚገልጸው፣ በኢያሱ የድል አድራጊነት አውድ ውስጥ እነዚህ ቃላት "ለመደምሰስ" የሚለውን ትርጉም ብቻ አይይዙም፡፡ ይልቁኑ፣ "ለእግዚአብሔር ፈጽሞ ለመለየት" ወይም "ለእግዚአብሔር ፈጽሞ ለመቀደስ መደምሰስ የሚል ትርጓሜ ይኖራቸዋል፡፡ ስለዚህ፣ እስራኤላውያን በከነዓን ምድር ውስጥ ውጊያ ሲያደርጉ፣ በከነዓናውያን እጅግ የከፋ ኃጢአት ላይ የእግዚአብሔር ፍትሃዊ ፍርድ ለማረፉ ማሳያ ነው፡፡ እናም ድል ባደረጉበት ስፍራ ሁሉ የሚያገኙትን ሁሉ ፈጽሞ በማጥፋት ለእግዚአብሔር ፈጽሞ በመቀደስ እግዚአብሔርን በማምለክ ያከብሩታል፡፡

በዘመነ ኢያሱ ፈጽሞ የማጥፋቱና ለጌታ የመቀደሱ ትዕዛዝ አምሳያ የማይገኝለት ሆነው በበርካታ ምክንያቶች እንደሆነ እናውቃለን፡፡ አንደኛው፣ በዘዳግም 20፡10-20፣ ላይ ሙሴ ከነዓናውያንን ፈጽመው እንዲያጠፉ ሲያዝዝ፣ ነገር ግን ከከነዓን ምድር ውጪ ከሚኖሩት ህዝብ ጋር በሰላም እንዲኖሩ እስራኤላውያንን አዝዟል፡፡ በምዕራፍ 9 ላይ እንደምናነብበውም ገባዖናውያን ከከነዓን ምድር ውጪ እንደመጡ ኢያሱ በማመኑ ቃል ኪዳን ሲገባ ለዚህ ልዩነት እውቅና እንደሰጠ እንገነዘባለን፡፡

ከዚህም በተጨማሪ፣ የኢያሱ ድል አምሳያ የሌለው የመሆኑ ነገር በግልጽ የታየው በእግዚአብሔርና በሰይጣን መካከል ያለው ዘላቂ ውጊያ፣ ከኢያሱ ቀድሞም ሆነ ከእርሱ በኋላ፣ በተለያየ መንገድ እንዴት እንደቀጠለ ስናስተውል ነው፡፡ ጥቂት ምሳሌዎችን ለማንሳት ያህል፣ ከኢያሱ አስቀድሞ፣ በዘፍጥረት 11፡1-9 እንደምናነብበው፣ እግዚአብሔርና የመላእክት ሠራዊቱ ከአመፀኞቹ የሰው ልጆች ጋር ባቢሎን ግንብ እንደተዋጉ እናያለን፡፡ ይህንን ያደረጉት ግን ያለ ሰብዓዊ ሠራዊት ህዝቡን በመበተን ነበር፡፡ በዘፍጥረት 14፡1-24፣ አብርሃም በእግዚአብሔር እርዳታ ተዋግቷል፣ ነገር ግን አብርሃም ጠላቶቹን ፈጽሞ እንዲደመስስ እግዚአብሔር አላዘዘም፡፡ በዘፀአት 12፡12 ውስጥ፣ እግዚአብሔር በግብጽ ምድር ላይ መቅሰፍትን ሲመጣ ከብጻውያን አማልክት ጋር እንደተዋጋ እንገነዘባለን፡፡ ነገር ግን እስራኤላውያን ምንም ያደረጉት አልነበረም እግዚአብሔርም ግብጻውያንን ሁሉ አልገደለም፡፡ በዘፀዓት 14 ውስጥ፣ በቀይ ባህር ውስጥ፣ እስራኤላውያን ለውጊያ በመዘጋጀት እግዚአብሔርን ፈጽመው በመታዘዝ ተከትለው ነበር፣ የግብጻውያንን ሠራዊት የደመሰሰው ግን እግዚአብሔር ነበር፡፡

ተመሳሳይ የሆኑ በርካታ ውጊያዎችም ከኢያሱ ዘመን በኋላም ተከናውነዋል፡፡ ዳዊት በእግዚብሔር መለኮታዊ እርዳታ ከበርካታ የእስራኤል ጠላቶች ጋር እንደተዋጋ፣ የሳሙኤል መጽሐፍ ማብራሪያ ይሰጠናል፡፡ ሆኖም ግን እግዚአብሔር ጠላቶቹን ሁሉ ጨርሶ አልደመሰሳቸውም፡፡ የነገሥት መጽሐፍ እንደሚያሳየን የዳዊት ንጉሣዊ ዝርያዎችም ይኸው ተመሳሳይ ውጊያ ገጥሟቸዋል፡፡ የእስራኤል ነቢያት እንደተናገሩትም የእስራኤላውያን የግዞት ዘመን ማብቂያም ወደር በማይገኝለት በመለኮታዊ ጣልቃ ገብነት በሚከናወን ጦርነት አማካይነት እንደሚከናወን እንረዳለን፡፡

እግዚአብሔር ከክፉው ጋር የሚያደርገው ዘላቂ ፍልሚያ በፔንታቱክ እና በብሉይ ኪዳን በጠቅላላ በተለያዩ መንገዶች እንደሚከናወን መመልከት እንችላለን፡፡ ይህም የሚያሳየን የኢያሱ ድል የሁሉም ጦርነቶች ናሙናና መለኪያ ሊሆን እንደማይችል ነው፡፡ እርግጥ ነው፣ ቀደምት ተደራሲያኑ በዘመናቸው ለሚገጥማቸው ጦርነት ከኢያሱ የሚማሩት በርካታ

ነገር ይኖራቸዋል፡፡ ድሉ በራሱ ግን ወደር የማይገኝለት የእግዚአብሔር ፍርድ ወቅት ነበር፡፡ ከሌሎቹ ጦርነቶች ለየት ባለ መንገድ፣ ረዓብን ከመሳሰሉ አንዳንድ ሰዎች በስተቀር፣ ከነዓናውያንን ጨርሶ ለመደምሰስ እግዚአብሔር ወስኖ ነበር፡፡

*የከነዓናውያን ኃጢአት ቀስ በቀስ በጊዮ ብዛት እጅግ አስቃቂ ወደሚሆንበት ደረጃ ላይ ደርሶ ነበር፡፡ በዘፍጥረት መጽሐፍ ማለትም በዘፍጥረት 15 ውስጥ፣ የአሞራውያን ኃቲአት ጽዋው እስኪሞላ ድረስ የተባለው መግለጫ ይህ እንደሆነ አምናለሁ፡፡ የእግዚአብሔር ህዝብ ይህ እኪፈጸም ድረስ ምድራቸውን አልወረሱም ነበር፡፡ ስለዚህ፣ እግዚአብሔር የከነዓናውያን ኃጢአት የዝቅጠቱ ጣሪያ ላይ እስኪደርስ ድረስ በአንክሮ ይመለከታቸው እንደነበርና ኃጢአታቸውም ዘቅጦ ከመጨረሻው የዝቅጠት እርከን ላይ ሲደርስ እግዚአብሔር ፍርዱን ያፈሰሰባቸዋል የሚል ሀሳብ ያዘለ ነው፡፡ የዚህ ፍትሁ ማስፈጸሚያ ደግሞ የእስራኤል ህዝብ ነበር፣ ሆኖም ይህ ሆነበት ምክንያቱ እስራኤል ከፍተኛ የሞራል ልዕልና ስነበራት ወይም ተመሳሳይ ለዚህ የሚያበቃ ነገር ስለነበራት አልነበረም፡፡ እነርሱ እጅግ ታናሽ ህዝብ ነበሩ፡፡ በደላቸውም እጅግ የከፋ ነበር፣ ከኢያሱ ቀድሞ የነበረውም ትውልድ በኃጢአቱ እጅግ የከፋ ነበር፣ ድል በሚያደርጉበትም ወቅት ኃጢአት ሠርተው ነበር፡፡ የጉዳዩ እውነታ ግን እግዚአብሔር፣ በጺጋው በዚያ ይኖሩ የነበሩትን ነገሥታት ከዚያ ለማጥፋት ያንን ህዝብ ጠራ ተጠቀመባትም፡፡ እነዚያ ህዝብ በዚያ እንዲኖሩ ከተዋቸው፣ እነርሱን ማርከሳቸው አይቀሬ ነው፡፡ እስራኤላውያን ወደ ከነዓን ምድር በመምጣት በዚያ በህይወት ያለውን ሁሉ እንዲያጠፉ እግዚአብሔር ያዘዘበት ሌላኛው ምክንያት ይህ ነበር፡፡ የእርሱ ህዝብ እዚያ ይኖሩ በነበሩ ሰዎች ሃይማኖታዊ ልምምድ፣ በጣዖቶቻቸው፣ እንዲረከስ አልፈቀደም፣ ደግሞም የእርሱ ህዝብ በዙሪያቸው እንዳሉ መንግስታት ወግ እንዲሄዱ እግዚአብሔር አልፈቀደም፡፡ እርሱን ንጉሣቸው አድርገው፣ እርሱን እንዲከተሉ ይፈልግ ነበር፡፡ እስራኤላውያንም ወደዚያ ገቡ፣ ሆኖም ግን የተሰጣቸውን ተግባር ሙሉ በሙሉ አልፈጸሙም፡፡ በራሱ በኢያሱ መጽሐፍ ውስጥ የነገሩን ፍንጭ እናስተውላለን፣ ያም ፍንጭ ከመሳፍንት ዘመን በኋላ እስራኤል እጅግ እየረከሰች ደግማ ደጋግማ በኃጢአት ቀለበት ውስጥ እየተሽከረከረችና እየዘቀጠች መሄዷ ይበልጥ ተብራርቶ ተጽፏል፡፡ በዚህም ምክንያት እስራኤል ከእግዚአብሔር ጋር ካላት የቃል ኪዳን ግንኙነት መገለጫ እየራቀች፣ በዙሪያዋ እንዳሉት የአህዛብ መንግሥታት እየመሰለች ሄደች፡፡ እነዚያ መንግሥታት ግን እስራኤል ጨርሳ እንድታጠፋቸው እግዚአብሔር ያዘዛት መንግሥታት ነበሩ፡፡*

*ሬቨረንድ ኬቪን ላቢ*

**የእስራኤል ንጉሥ የወደፊት ድል፡፡** በሦስተኛ ደረጃ፣ ጸሐፊአችን በተጨማሪም የኢያሱ ድል ወደፊት የሚመጣው የእስራኤል ንጉሥ ድል የመጀመሪያ እርከን እንደሆነ ከፔንታቱክ ባገኘው መረጃ ያውቅ ነበር፡፡ ያም ንጉሥ በመላው ዓለም ላይ ለዘላለም ይነግሣል ተብሎ በናፍቆት የሚጠበቀው ንጉሥ ነው፡፡ ቀደም ብሎ፣ ከአበው መካከል የሆነው ያዕቆብ በዘፍጥረት 49፡10 ላይ፣ የይሁዳ የነገሥታት ዝርያ "አህዛብ ይታዘዙታል" በማለት ያውጃል፡፡ በመሳፍንት ዘመን፣ ለይሁዳ የነገሥታት ዝርያ የተሰጠው ተስፋ በመሳፍንት 1፡1 እና 2 በተመዘገበውና ለይሁዳ ነገድ በተሰጠው የመሪነት ሃላፊነት እውቅና ተሰጥቶታል፡፡ በነገሥታቱ ዘመን፣ የዚህ ትንቢት ፍጻሜ ከዳዊት ቤት ጋር በቀጥታ እንደተገናኘ መዝሙር 72 በመሳሰሉ ስፍራዎች ተጠቅሷል፡፡ በበርካታ ምንባቦች ደግሞ፣ የዳዊት ልጅ አህዛብን ሁሉ ሲገዛ ግዞቱ እንደሚያበቃ በርካታ ነቢያት ተንብየዋል፡፡

ስለዚህ፣ በኢያሱ ዘመን እንደነበሩት እስራኤላውያን ሁሉ፣ የቀደሙት ተደራሲያን ከእርሱ የዘለለ የአንድ ትልቅ ነገር አካል እንደሆኑ ያውቁ ነበር፡፡ እናም በዚህ ምክንያት፣ እንዲያው ዝም ብለው ኢያሱ ባከናወነው ነገር እየኮሩ በቀደመ ዘመን ታሪክ ብቻ ሊመላለሱ አይችሉም፡፡ ከነዓንን ድል ለማድረግ የተከናወነውን ተግባር በራሳቸውም ዘመን ተግባራዊ በማድረግ የእስራኤል ንጉሥ በመላው ዓለም ላይ ወደፊት ወደሚቀዳጀው ድል የሚያመራው ታሪክ አካል ሆነው መቀጠል አለባቸው፡፡

## የነገዶች የርስት ክፍፍል

ጸሐፊአችን በሁለተኛው የመጽሐፉ ክፍል ውስጥ ስለ እስራኤል ነገዶች ክፍፍል ካለው ነገረ-መለኮታዊ አመለካከት ጋር የሚስማማ አመለካከት ተደራሲያኑም እንዲኖራቸው ይጠብቃል፡፡

***ጥንት ፍጥረተ-ዓለማዊ የሰው ዘር ገዢነት፡፡*** በመጀመሪያ ደረጃ፣ እስራኤላውያን ከነዓንን የመውረሳቸው ነገር የሰው ዘር ምድርን እንዲገዛ እግዚአብሔር በጥንት ፍጥረተ-ዓለማዊ ዘመን ከሰጠው ጥሪ ጋር የተሳሰረ መሆኑን ከሙሴ መጻሕፍት ይገነዘባል፡፡ ምድር በእግዚአብሔር አምሳል ስትሞላና ስትገዛ ምድር ወደ እግዚአብሔር መንግሥትነት እንደምትለወጥ ገና ከጥንት ፍጥረተ-ዓለም ጀምሮ እግዚአብሔር ወስኗል፡፡ ይህ ጥሪ ለመጀመሪያ ጊዜ የተመዘገበው በዘፍጥረት 1፡26-30 እና በኋላ ደግሞ በዘፍጥረት 9፡1-3 ተደግሞ ተረጋግጧል፡፡ እንግዲያው፣ በመጽሐፈ ኢያሱ ተመዝግቦ የምናገኘው የእስራኤል ነገዶች የርስት ክፍፍል ለቀደሙት ተደራሲያን ግልጽ አግባብነት አለው፡፡ ልክ በኢያሱ ዘመን እንደነበሩ እስራኤላውያን፣ የቀደሙት ተደራሲንያንም የሰው ዘር ምድርን እንዲገዛ እግዚአብሔር በሰጠው ተልዕኮ ውስጥ ተካፋይ ናቸው፡፡

***የእስራኤል ልዩ ውርስ፡፡*** በሁለተኛ ደረጃ፣ ጸሐፊአችን የእስራኤልን ልዩ ውርስ አስቀድሞ እንደመሠረተው ከፔንታቱክ መጽሐፍ በትክክል ተገንዝቧል፡፡ በኢያሱ ዘመን ለእስራኤል ነገዶች የተደረገው የመሬት ክፍፍል የዚህን የውርስ ቃል ኪዳን ፍፃሜ የመጀመሪያ ክፍል የሚያመለክት ነው፡፡ ለአብነትም፣ በዘፍጥረት 15፡18-21 ውስጥ፣ ከግብጽ ጀምሮ እስከ ኤፍራጥስ ወንዝ ድረስ ያለውን ምድር ለእርሱና ለዘሩ እንደሰጠ እግዚአብሔር ለአብርሃም ተስፋን ሰጥቶታል፡፡ ስለዚህም፣ ከፔንታቱክ መዝገበ ቃላት እንደምንገነዘበው፣ መጽሐፈ ኢያሱ በተደጋጋሚ የእስራኤላውያንን የርስት ክፍፍል ሲጠቅስ የተጠቀመው “ናቻል” የተሰኘውን የዕብራይስጥ ግስ ሲሆን ትርጓሜውም “መውረስ” ማለት ነው፡፡ ሌላው ደግሞ፣ “ናቻላ” የተሰኘውን ስም ሲሆን ትርጓሜውም “ውርስ” ማለት ነው፡፡ ይህ ቃል የሚያመለክተው የእስራኤል ምድር ከእግዚአብሔር የተሰጠ ዘላቂ ውርስ መሆኑን ነው፡፡

በዚህ ምክንያት፣ የቀደሙት ተደራሲያን ኢያሱ ለየነገዶቹ ርስትን ከማከፋፈል አንጻር ካከናወነው ተግባር የሚማሩት በርካታ ትምህርት ይኖራል ማለት ነው፡፡ በመሳፍንት ዘመን፣ በእስራኤል ነገዶች መካከል የነበረው መከፋፈልና ከሌሎች ህዝቦች ጋር የነበራቸው ግጭት ኢያሱ ላስመዘገበው ስኬት ቀጣይነት እንቅፋት ሆነው ነበር፡፡ በነገሥታት ዘመን፣ የእስራኤል ነገሥታት የእስራኤልን ድንበር አስፋፍተዋል፣ ነገር ግን በተቃራኒው በርካታ እንቅፋቶችና ኪሳራዎችም ነበሩባቸው፡፡ በእርግጥም፣ በባቢሎን ምርኮ ዘመን፣ በምድሪቱ ላይ ቀርተው የነበሩት ጥቂት የእግዚአብሔር ህዝብ ቅሬታዎች ብቻ ነበሩ፡፡ በዚያ የነበሩትም በሌሎች መንግሥታት አምባገነናዊ የጭቆና አገዛዝ ስር ነበር፡፡ ስለዚህ፣ ኢያሱ ለእስራኤል ነገዶች ያደረገው የርስት ክፍፍል ለቀደሙት ተደራሲያን ትልቅ ትምህርት በረው ሲሆን በራሳቸው ዘመን እግዚአብሔር እያመለኩ ከመኖር አንጻር ያለው ፋይዳ የጎላ ነበር፡፡

***የወደፊቱ የእስራኤል ንጉሥ ውርስ፡፡*** በሦስተኛ ደረጃ፣ እስራኤልን የከነዓንን ምድር መውረሷ፣ የወደፊቱ የእስራኤል ንጉሥ ለሚወርሰው ውርስ የመጀመሪያ እርከን ሆኖ እንደሚቆጠር ጸሐፊአችን ጠንቅቆ ያውቃል፡፡ ዘመኑ ሲደርስ፣ ታላቁና ጻድቁ የእስራኤል ንጉሥ እያንዳንዱን ምድርና ህዝብ ይወርሳል ያንንም ሲደርግ አስቀድሞ ለሰው ዘር ተሰጥቶ የነበረውን ምድርን የመሙላትና የመግዛት ጥሪ ከፍጻሜ ያደርሳል ማለት ነው፡፡ ቀደም ብለን እንደጠቀስነው፣ ከይሁዳ ነገድ የሆነው ንጉሥ “የአህዛብ መታዘዝ ለእርሱ እስከሚሆን ድረስ” እንደሚነግሥ ዘፍጥረት 49፡10 ያውጃል፡፡ በተጨማሪም፣ በዘፍጥረት 17፡4 ውስጥ፣ “ለብዙ አህዛብም አባት ትሆናለህ” በማለት እግዚአብሔር ለአብርሃም ተስፋ ሰጥቶታል፡፡ በመዝሙር 2፡8 ውስጥ፣ “አህዛብን ለርስትህ የምድርንም ዳርቻ ለግዛትህ እሰጣለሁ” በማለት በተለይ ለዳዊት ቤት እግዚአብሔር የተናገረው ለዚህ ነበር፡፡ የዳዊት ልጅ ግዛቱ ከአንዱ የምድር ጫፍ እስከ ሌላኛው የምድር ጫፍ ድረስ እንደሚሆን የእስራኤል ነቢያት በርካታ ጊዜ አውጀዋል፡፡ ይህንን የብሉይ ኪዳን አመለካከት፣ ጳውሎስም በሮሜ 4፡13 ውስጥ “የዓለምም ወራሽ እንዲሆን ለአብርሃምና ለዘሩ የተሰጠው የተስፋ ቃል” በማለት ጠቅለል አድርጎ አስቀምጦታል፡፡ በዚህ ረገድ ጸሐፊአችን ለቀደምት ተደራሲኑ የሚያስቀምጠው አንድምታ ግልጽ ነው፡፡ በኢያሱ መጽሐፍ ውስጥ የሚያነብቡትን ነገር በራሳቸው ዘመን ተግባራዊ በማድረግ እግዚአብሔር ወደዚህ ዓለም አቀፋዊ ውርስ ህዝቡን እየመራ የሚያደርስባቸውን መንገዶች ማስተዋል ይገባቸዋል ማለት ነው፡፡

> **በሮሜ 4 ውስጥ ሐዋርያው ጳውሎስ ለአብርሃምና ለዘሩ የተሰጠው የውርስ ተስፋ ዓለምን ሁሉ እንደሚጠቀልል በግልጽ ትርጓሜ እንዳስቀመጠው እናያለን፡፡ መጀመሪያ ስንመለከተው እኛን ሊያስደንቀን ይችላል፡፡ ስለ ተስፋዪቱ ምድር ስናስብ የምናስበው በሜዲትራኒያን ባህር ምሥራቃዊ ጠርዝ ላይ ስለምትገኝ አንድ የሪል ስቴት ሰርጥ ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን የተስፋው ቃል ሉል አቀፍና ዓለምን ሁሉ የሚጠቀልል እንደሆነ ጳውሎስ ከተረዳው መረዳት ጋር ስናስተያየው እጅግ በጣም ትንሽ ነው፡፡ ደግሞ ደጋግሞ ስለ ዘር፣ ስለ አብርሃም ልጆች፣ የሥጋ ልጆቹ ስለሆኑት ብቻ ሳይሆን፣ ነገር ግን የአብርሃምን ፈለግ የሚከተሉ፣ ያም፣ የእርሱን የእምነት ፈለግ በመከተል በእግዚአብሔር**

***ተስፋዎች የሚታመኑትን ሁሉ በማካተት ይናገራል፡፡ እንዲያውም፣ ጳውሎስ በገላትያ 3 ማብቂያ ላይ፣ አይሁድ ብቻ ሳይሆኑ በክርስቶስ ያመኑት አህዛብም ጭምር የእግዚአብሔር የተስፋ ቃል ወራሾችና የአብርሃም ዝርያዎች እንደሆኑ አጽንዖት ሰጥቶ ይጠቅሳል፡፡ ስለዚህ ጳውሎስ በሮሜ 4 ውስጥ፣ በእምነት፣ የአብርሃም ልጆች የሆኑት ሁሉ፣ ዓለምን ሁሉ ይወርሳሉ፣ ሲል ይህንኑ ተመሳሳይ መረዳት እያንጸባረቀ ነው፡፡***

**ዶ/ር ዴኒስ ጆንሰን**

## በቃል ኪዳን መታመን

ልክ እንደ መጀመሪያውና እንደ ሁለተኛው የመጽሐፋችን ክፍል ሁሉ፣ የዚህም የሦስተኛው የመጽሐፈ ኢያሱ ክፍል ማለትም እስራኤል በቃል ኪዳን እንድትታመን የቀረበላትን ጥሪ ቀደምት ተደራሲያኑ ከፔንታቱክ ባገኙት ነገረ-መለኮታዊ አመለካከት መሰረት በመቃኘት በዘመናቸው ተግባራዊ እንዲያደርጉ ጸሐፊው ይጠብቅብቻዋል፡፡

***የጥንት ፍጥረተ-ዓለማዊ የሰው ዘር ታማኝነት፡፡*** በመጀመሪያ ደረጃ፣ በቃል ኪዳን መታመን ገና በፍጥረተ ዓለም የሰው ዘር ለእግዚአብሔር ታማኝ እንዲሆን ከተሰጠው ትዕዛዝ ጋር የተያያዘ እንደሆነ ጸሐፊአችን ከፔንታቱክ ይገነዘባል፡፡ በቀላሉ የእግዚአብሔር አምሳሎች መሆናችን ከእግዚአብሔር ጋር በቃል ኪዳን ያስተሳስረናል፣ ይህም ትስስር እርሱን በታማኝነት ማገልገልን ይጠይቃል፡፡ በአዳም አማካይነት እግዚአብሔር ከሰው ዘር ሁሉ ጋር የገባው ቃል ኪዳን በዘፍጥረት 1-3 እና ሆሴዕ 6፡7 እንደተገለጸው፣ መታዘዝን ይጠይቃል፡፡ ደግሞም በዘፍጥረት 6፡9 የተገለጸው፣ እግዚአብሔር ለኖህ የገባው ቃል ኪዳን የሰው ዘር በሙሉ እግዚአብሔርን በቃል ኪዳን እንዲያገለግል ያነሳሳል፡፡ ይህ እውነት በሁሉም ዘመን ለሚኖር ህዝብ ሁሉ ሚራ ስለሆነ፣ ኢያሱ በራሱ ዘመን በቃል ኪዳን ስለመታመን ካቀረበው ጥሪ ቀደምት የሆኑት ተደራሲያን ብዙ የሚማሩት ነገር አለ፡፡ እነርሱም፣ እንደተቀሩት የሰው ልጆች ሁሉ፣ ለእግዚአብሔር የታመነ አገልግሎት ሊሰጡ ይገባቸዋል፡፡

***የእስራኤል ልዩ ታማኝነት፡፡*** በሁለተኛ ደረጃ፣ የቀደሙት ተደራሲያን ስለ እስራኤል በቃል ኪዳን ልዩ መታመን ሊያውቁም ይገባል፡፡ ጸሐፊአችንም ጉዳዩን የሚዘግበው በጥንቃቄ ነው፡፡ በድል አድራጊነት በሚወርሱበት ዘመን፣ ህዝቡ ለእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ታማኝ ሆነው እንዲዘልቁ ኢያሱ ያሳስባቸው ነበር፡፡ ህዝቡም ያንኑ እንደሚያደርጉ ቃል ገቡ፡፡

በዘፍጥረት 17፡1 ውስጥ የሚገኘውንና እግዚአብሔር ከአብርሃም ጋር የገባውን ቃል ኪዳን የቀደሙት ተደራሲያን ያውቃሉ፡፡ በዚያም ህዝቡ ለእግዚአብሔር እንከን የሌለባቸው ሆነው ለመገኘት ያላቸውን መሰጠት ለማሳየት እንዲገረዙ ያዛል፡፡ በዘጸአት 19-24 ውስጥ ደግሞ እግዚአብሔር ለሙሴ በሰጠው እና በዘዳግም መጽሐፍ በታደሰው ቃል ኪዳን ደግሞ፣ እስራኤል የሙሴን ህግ ልትፈጽም እንደሚገባ በግልጽ ያስቀምጣል፡፡ አሁን ደግሞ፣ በዚህ በሦስተኛው የመጽሐፋችን ክፍል፣ እስራኤል እነዚህን የቃል ኪዳን ግዴታዎች ይጠብቁ አይጠብቁ እንደሆነ የተለያዩ መፈተኛዎች በማቅረብ፣ በተለይም የሃሰት አማልክትን ቸል ከማለት አንፃር ያሉትን አስመልክቶ ኢያሱ ትኩረት ሰጥቶ ያሳስባቸዋል፡፡ በእነዚያ ረገድ ከታማኝነት ጎድለው ከተገኙ ሊገጥማቸው የሚችለውን ችግር፣ ሽንፈት እና ከተስፋዪቱ ምድር መሰደድ በግልፅ ያስቀምጥላቸዋል፡፡

የመጽሐፉ ቀደምት ተደራሲያን በኖሩበት ዘመን፣ እነዚያ ፈተናዎች ቀስ በቀስ መከሰት ጀመሩ፡፡ በመሳፍንት ዘመን ደግሞ፣ እስራኤላውያን በተያያዥ የችግር ሰንሰለት ውስጥ ገቡ፡፡ በነገሥታት ዘመን ደግሞ፣ በእስራኤል ላይ በርካታ ፍርዶች ወረዱባት ምክንያቱም ህዝቡና ነገሥታቶቹ በተደጋጋሚ ጣዖታትን በማምለክ ኃጢአት ውስጥ በመግባታቸው ነበር፡፡ በባቢሎን ምርኮ ዘመን ደግሞ፣ ከተስፋዪቱ ምድር የመፈናቀሉ ፈተና አሰቃቂ እውነታ ሆኖ ተከሰተ፡፡ ስለዚህ፣ ቀደምት ተደራሲያኑ በእነርሱ ዘመን ሊመጣባቸው ስለሚችለው የእግዚአብሔር ፍርድ አስቀድሞ ኢያሱ ለእስራኤል የሰጣቸውን ማሳሰቢያ በአንክሮ መመልከት ይገባቸዋል፡፡

***ከእስራኤል ንጉሥ ጋር የተገባው የወደፊት ቃል ኪዳን፡፡*** በሦስተኛ ደረጃ፣ በኢያሱ ዘመን የሆነው ነገር ወደፊት ከሚመጣው ከእስራኤል ንጉሥ ጋር እግዚአብሔር የገባውን ቃል ኪዳንም ያመለክታል፡፡ ከዘፍጥረት 49፡10 እንደምንረዳው፣ እግዚአብሔር ከይሁዳ ንጉሥን እንደሚስነሳ ያመለክታል፡፡ ደግሞም ዘፍጥረት 17፡6 እስራኤል ንጉሥ እንደሚኖራት ያመለክታል፡፡ ምንም እንኳን በመሳፍንት ዘመን እስራኤል ህጋዊ ንጉሥ ያልነበራት ቢሆንም፣ መሳፍንት 21፡25 እና በ1ኛ ሳሙኤል 2፡10 የተመዘገበውን የሃናን ጸሎት በመሳሰሉ ክፍሎች ውስጥ እንደምናየው በዚያም ዘመን እንኳን፣ የጣመኑት ሰዎች እግዚአብሔር ከሚስነሳው የእስራኤል ንጉሥ ዝርያ ትድግና እንደሚመጣላቸው በናፍቆት ይጠብቁ ነበር፡፡

እንግዲህ፣ የኢያሱ መጽሐፍ የተጻፈው በእስራኤል የነገሥታት ዘመን ወይም በባቢሎን ምርኮ ዘመን ከተጻፈ፣ ኢያሱ ለቃል ኪዳን ታማኝ ሆነው እንዲዘልቁ ያቀረበላቸውን ጥሪ እግዚአብሔር ከዳዊት ጋር ከገባው የንግሥና ቃል ኪዳን ጋር በማዛመድ ሊረዱት ይገባል፡፡ እንደ 2ኛ ሳሙኤል 7 እና መዝሙር 89፣ 132 በመሳሰሉት ምንባቦች ውስጥ፣ እግዚአብሔር ከዳዊት ጋር የገባው ቃል ኪዳን በታማኝነት አስፈላጊነት ላይ እንዳተኮረ እንመለከታለን፡፡ የዳዊት የነገሥታት ዝርያ ለእግዚአብሔር ታማኝ ሆኖ ሊዘልቅ ይገባዋል ምክንያቱም በእግዚአብሔር ፊት ህዝበ እስራኤልን ወክለው የሚቀርቡ ናቸውና፡፡

በተጨማሪም፣ በኢሳያስ 53፡11 በተቀመጠው ትንቢት መሠረት፣ "ጻድቁ የጌታ ባሪያ" የእስራኤል እንከን የማይገኝበት ንጉሥ፣ በሚያከናውነው ምትካዊ ሞት ምክንያት ዘላለማዊ ምህረት ወደፊት እንደሚገኝ በግልጽ ያመለክታሉ፡፡ ይህ ታላቅ ንጉሥ ግን ኤርምያስ በትንቢቱ በምዕራፍ 31 ውስጥ በተናገረው መሠረት አዲሱን ኪዳን ከሚያመጣው ከኢየሱስ ክርስቶስ በቀር ማንም ሊሆን አይችልም፡፡ ይህም ኪዳን ወደ ሙላቱ የሚደርሰውክርስቶስ ዳግም ሲመጣና ሁሉን አዲስ ሲያደርግ ይሆናል፡፡ ቀደምት ተደራሲያኑም ይህንን ኢያሱ ለቃል ኪዳን ታማኝ ስለመሆን ያቀረበውን ጥሪ በእርሱ ዘመን ሲያዛምዱ፣ ሊመለከቱት የሚገባው እግዚአብሔር በየዘመናቱ ከህዝቡ ጋር በገባቸው ቃል ኪዳኖች ግንባታ ሂደት ውስጥ በየትኛው ዘመን ላይ እንደቆሙ በማሰብ ነው፡፡

እንግዲህ፣ የመጽሐፈ ኢያሱን ቀደምት ትርጓሜ ለማግኘት በምንጥርበት ወቅት፣ ተደራሲያኑ በኢያሱ ዘመን ምን ምን እንደተከናወነ እንዲያስተውሉ ጸሐፊው በብርቱ የሚፈልግ መሆኑን ዘወትር ከግምት ውስጥ በማስገባት ሊሆን ይገባዋል ማለት ነው፡፡ ነገር ግን፣ ያንን ሲያደርጉ በድል አድራጊነት ስለመውረሳቸው፣ ስለ ነገዶች የርስት ክፍፍል እና በቃል ኪዳን ታማኝ ሆኖ ስለመዝለቅ ስላቀረበው ጥሪ ያሰፈረውን ዘገባ ከእነርሱ ዘመንና ሁኔታ ጋር በሚጣጣምባቸው መንገዶች እንዲሆንም ይፈልጋል፡፡

በመጽሐፈ ኢያሱ ላይ ያዘጋጀነውን ጥናት መግቢያ በምንመለከትበት ጥናታችን እስካሁን ድረስ ጸሐፊውንና ዘመኑን፣ እንዲሁም ንድፉንና ዓላማውን ተመልክተናል፡፡ አሁን ደግሞ ወደ ትምህርታችን ሦስተኛ ክፍል፤ ክርስቲያናዊ ተዛምዶ ወደ ተሰኘው ርዕስ እንሸጋገራለን፡፡ እኛ ዛሬ ክርስቶስን በምንከተልበት ወቅት የኢያሱ መጽሐፍ ተፅዕኖ ሊያሳድርብን ሚገባው እንዴት ነው? በሚል ሃሳብ እንመለከተዋለን፡፡

## ክርስቲያናዊ ተዛምዶ

በዕብራይስጥ፣ "ኢየሱስ" የሚለው ስም "ኢያሱ" ማለት ነው፡፡ ይህ ቀላል እውነታ፣ ከክርስቲያናዊ አመለካከት አንጻር፣ ኢየሱስ፣ በዘመነ ኢያሱ ተጀምሮ የነበረውን ነገር ፈጽሞታል ወይም ወደ ሙላት አምጥቶታል ማለት ነው፡፡ በብዙ መንገዶች፣ መጽሐፈ ኢያሱን ከእኛ ሕይወት ጋር በምናዛምድበት ወቅት ተዛምዶአችን ከዚህ ከክርስቶስ ወደ ሙላት ከማምጣቱ ሥራ የመነጨ ሊሆን ይገባዋል፡፡ በኢያሱና በኢያሱ መካከል ያለውን ግንኙነት ይበልጥ በተረዳን ቁጥር፣ ይህ መጽሐፍ እንደ ክርስቶስ ተከታዮች ሊያሳድርብን የሚገባውን ተጽእኖ ይበልጥ እየተረዳን እንሄዳለን፡፡ እንደተመለከትነው፣ የመጽሐፉ ጸሐፊ በኢሱ መሪነት ስለተከናወነው ስለ እስራኤላውያን በድል መውረስ፣ ስለ ነገዶች የርስት ክፍፍል እና ለቃል ኪዳን ታማኝ ሆኖ ስለ መዝለቅ ሲጽፍ ዓላማው መጪውን የእስራኤል ትውልድ መንገድ ማሳየት ነበር፡፡ ሆኖም ጸሐፊአችን ያንን የወደፊት ጊዜ ሲያመለክት፣ የእስራኤል ንጉሥ እንደሚመጣ፣ በኢያሱ መጽሐፍ የተነገሩትን ግቦች ደግሞ እንደሚያሳካም ጭምር በመገንዘብ ነበር፡፡

> ***ኢያሱ እነዚያን በድል የታጀቡ ውጊዎች ሲመራ፣ ህዝቡ የተስፋውን ምድር እንዲወርስ በማድረግ ነበር ይመራ የነበረው፡፡ ውድቀት ሲገጥማቸውና ኃጢአትን ሲሩ ደግሞ ስለ ህዝቡ የሚሟገት ጠበቃ ሆኖ ይቆም ነበር፡፡ ለህዝቡ እየማለደ ተስፋ የተሰጠውን ህዝቡን ወደ ተስፋዪቱ ምድር ይመራ ነበር፡፡ ይህም በጠቅላላው የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስን ምስል የሚያመለክት ነው፡፡ በዕብራውያን ምእራፍ 4 እንደተጠቀሰው፣ ክርስቶስ የእግዚአብሔርን ህዝብ ተስፋ ወደተገባላቸው ርስት ይመራል፡፡ ስለ እግዚአብሔር ህዝብ ጥብቅና ይቆማል፣ ስለ ህዝቡ ይጸልያል ስለ ህዝቡ ይማልዳል ደግሞም ለአዲስ ኪዳኗ የእግዚአብሔር ህዝብ፣ ማለትም ለጌታ ለኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን የሊቀ ካህንነት ተግባሩንም ያከናውናል፡፡ እነዚህ ሁሉ ምስሎች በአዲስ ኪዳን ዘመን ስለሚሆነው ነገር የሚያስረዱ ናቸው፡፡*** ***ሬቨረንድ ሄነሪ ቱርካኒክ፣ ትርጉም***

ሰፋ ባለ መልኩ ስናቀርበው፣ ኢየሱስ እንደ እስራኤል መሲህነቱ፣  እነዚህን ግቦች በብዙ መንገዶች ፈጽሟቸዋል፡፡ በመጀመሪያ፣ እስራኤል በኢያሱ ዘመን ያሳካቻቸውን መልካም ነገሮች ከኢየሱስ ጋር ስናስተያያቸው ማለትም፣ ከነዓንን መውረሷ፣ የተስፋቱን ምድር መውረስ የመጀመሪው እርከን፣ እና እስራኤል እግዚአብሔርን በቃል ኪዳን በመታመን ምምለኳን ስናይ፣ ኢየሱስም እንዴት ሁሉንም ወደ ፍጽምና እንዳመጣቸውና እንዳሳካቸው እናያለን፡፡ ሁለተኛ ደግሞ፣ የኢሱስን ድል ከእስራኤል ውድቀት ጋር በምናነጻጽርበት ወቅት ማለትም፣ አጥፉ ተብለው የታዘዙትን ከነዓናውያንን ጨርሰው አለማጥፋታቸውን፣ በነገዶች የርስት ክፍፍል ወቅት እርስ በርስ መጣላታቸውንና ቸል ማለታቸውን፣ ደግሞም ለእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ታማኝ ሆነው መዘለቅ አለመቻላቸውን ስንመለከት እነዚህን ሁሉ የእስራኤል ውድቀቶች ኢየሱስ እንዴት እንደቀለበሳቸው እናስተውላለን፡፡ በዚህም መንገድ፣ ኢየሱስ ምድርን ሁሉ ድል አደረገ፣ ሁሉን  ነገር ወረሰ፣ በመላው ዓለም በሁሉም ስፍራ በቃል ኪዳን ታማኝ መሆንን ስርዓትም መሠረተ፡፡

ነገር ግን፣ ዛሬ በዚህ ዘመን መጽሐፈ ኢያሱን እንዴት በክርስቲያናው ተዛምዶ መቃኘት እንደሚገባን ለመረዳት፣ አንድ ነገር ማስታወስ ይገባናል፡ እነዚህ በመሲሁ ወደሙላት የሚመጡ ግቦች የሚከናወኑት በጊዜ ርዝመት እንዲሆን እግዚአብሔር የወሰነ መሆኑን ነው፡፡

የብሉይ ኪዳንን ትንቢቶች መሠረት በማድረግ፣ በፓለስታይን ይኖሩ የነበሩ የመጀመሪው ምዕተ ዓመት አይሁዶች መሲሁ መጥቶ ሉል አቀፋዊ ድል ይቀዳጃል፣ ዓለምን ይወርሳል ደግሞም በየስፍራው ለቃል ኪዳን ታማኝ መሆንን ይመሠርታል ብለው በትክክል ያምኑ ነበር፡፡ ነገር ግን እነዚያው አይሁዶች ይህንን የሚያደርገውም በፍጥነትና በቅጽበት እንደሆነም ያምኑ ነበር፡፡ በተቃራኒው ግን፣ ኢየሱስና የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች ደግመው ደጋግመው እንዳብራሩት ኢየሱስ የሚመሠርተው መንግሥት እርስ በእርሳቸው በተያያዙ በሦስት እርከኖች ወደ ሙላት የሚመጣ ነው፡፡

የኢያሱን መጽሐፍ ክርስቲያናዊ ተዛምዶ በትክክለኛው መንገድ ለመረዳትና ለመገንዘብ የመንግሥቱን እርከኖች ለየብቻቸው መቃኘት ያስፈልጋል፡፡

## አጀማመር/አዋጅ/ብሥራት

በመጀመሪያ፣ ኢየሱስ በመንግሥቱ ጅማሬ ላይ ያሳካቸውን ነገሮች በመመርመር በመጽሐፈ ኢያሱ ተጀምረው የነበሩትንና ሙላታቸው ሲጠበቅ የነበረውን ክርስቶስ እንዴት እንደፈጸማቸው እንመለከታለን፡፡ ሁለተኛ፣ በመንግሥቱ ቀጣይነት ደግሞ በመጽሐፈ ኢያሱ የተነገረውን እንዴት እንደፈጸመው እንዳስሳለን፡፡ ሦስተኛ ደግሞ፣ ኢየሱስ በታላቅ ክብር ሲመለስ፣ በመንግሥቱ ፍጻሜ ወቅት ምን ምን ነገሮችን እንደሚያከናውን እንመረምራለን፡፡ አስቀድመን የክርስቶስን መንግሥት አጀማመር እንመልከት፡፡

### በድል አድራጊነት መውረስ

ኢየሱስ የጀመረው የእግዚአብሔር መንግሥት በመላው ዓለም ላይ ለሚቀዳጀው ክብርን የተሞላ ድል አድራጊነት የመጀመሪያ እርከን እንደሆነ አዲስ ኪዳን በበርካታ ስፍራዎች ያስተምራል፡፡ ሆኖም በኢያሱ መጽሐፍ የምናገኘውን የእስራኤልን በድል አድራጊነት የመውረስ ታሪክ ከኢየሱስ የመጀመሪያ ድል ጋር ስናነጻጽረው ግን፣ ግልጽ ልዩነት እናስተውላለን፡፡ ልክ ኢያሱ እንዳደረገው ቁሳዊ ሰይፍ ከማንሳት ይልቅ፣ ኢየሱስ የተጠቀመው መንታ ስልት ነበር፡፡ የጀመረው ሰይጣንንና አጋንንቶቹን ድል በማድረግ ነበር፡፡ ከዚያ ደግሞ ለሰው ዘር ሁሉ ወንጌልን ወይም የመንግሥቱን "የምሥራች" በማወጅ፣ ስለሚመጣው ፍርድ በማስጠንቀቅ ወደ እግዚአብሔር ምህረት እንዲቀርቡ ጥሪ አድርጎላቸዋል፡፡

ኢየሱስ በዮሐንስ 12፡31 እና 32፣ "የዚህ ዓለም ገዥ ወደ ውጭ ይጣላል፤ እኔም ... ሁሉን ወደ እኔ እስባለሁ።" በማለት ሲናገር፣ ይህንን መንታ ስልት ገልጾታል፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ በቆላስይስ 2፡15 ውስጥ "አለቅነትንና ሥልጣናትን ገፎ፥ ድል በመንሣት በእርሱ እያዞራቸው በግልጥ አሳያቸው።" በማለት ሲናገርና በተጨማሪም በኤፌሶን 4፡8 ላይ "ወደ ላይ በወጣ ጊዜ ምርኮን ማረከ ለሰዎችም ስጦታን ሰጠ።" በማለት የኢሱስ ሞት የዚያ ጅማሬ መሆኑን ያሳያል፡፡

**የነገዶች ርስት ክፍፍል**

አዲስ ኪዳን በተጨማሪም የክርስቶስ መንግሥት አጀማመር ወደፊት በሙላት የሚመጣውን የእግዚአብሔር ህዝብ ዓለምን የመውረሱን ተስፋ እንዴት ወደሙላት እንዳመጣው በሁለት አመለካከቶች ላይ አፅንኦት በመስጠት ያብራራል፡፡ በአንድ በኩል፣ ዕብራውያን 1፡2 "ሁሉን ወራሽ ባደረገው ደግሞም ዓለማትን በፈጠረበት በልጁ በዚህ ዘመን መጨረሻ ለእኛ ተናገረን (እግዚአብሔር)፤" በማለት ያብራራዋል፡፡ በማቴዎስ 28፡18 ደግሞ፣ "ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ" በማለት ኢየሱስ ውርሱን እንደተቀበለ ለደቀመዛሙርቱ ነግሯቸዋል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ፣ ኢየሱስ መንፈስ ቅዱስን በቤተክርስቲያን ላይ ሲያፈስስ ወደፊት የሚመጣውን ዓለምን የመውረስ ተስፋ ሁሉም እንዲቀምሱት እንዳደረገ አዲስ ኪዳን አፅንዖት ሰጥቶ ዘግቦታል፡፡ ኢሳያስ 44፡3 እና 4 የመሳሰሉ ትንቢቶችም እንደሚያመለክቱት፣ በመንፈስ ቅዱስ መውረድ አንድ ቀን ፍጥረት ሁሉ ይታደሳል፡፡ እንግዲያው፣ በኤፌሶን 1፡14፣ በቤተክርስቲያን ላይ የመንፈስ ቅዱስ መውረድ፣ "የርስታችን መያዣ" እንደሆነ ጳውሎስ የተናገረው ለዚህ ነው፡፡ ደግሞም፣ በ2ኛ ቆሮንቶስ 1፡22 እና 5፡5 ውስጥ፣ መንፈስ የሚመጣው ማለትም በአዲስ ሰማይና በአዲስ ምድር የምንቀበለው ርስታችን "መያዣ" ነው በማለት አስቀምጦታል፡፡

**በቃል ኪዳን መታመን**

በተጨማሪም፣ አዲስ ኪዳን የክርስቶስ መንግሥት ጅማሬ በሚያመጣው የአዲስ ኪዳን ዘመን በረከት በቃል ኪዳን መታመንን ልዩ አፅንዖት እንደሰጠው ያውጃል፡፡ በኤርምያስ 31፡1 ላይ የታወጀውን የአዲስ ኪዳን ትንቢት በመጥቀስ፣ በሉቃስ 22፡20 ውስጥ ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ እንዲህ ብሏቸዋል፡ "ይህ ጽዋ ስለ እናንተ በሚፈሰው በደሜ የሚሆን አዲስ ኪዳን ነው።" ኢየሱስ በመስቀል ላይ የእግዚአብሔርን የዘላለም ፍርድ መውሰዱንና ያም በእውነት ለሚያምኑ ሁሉ ስርየት እንደሆነላቸው የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች በግልጽ አስቀምጠውታል፡፡

ሆኖም ግን በዚህ በመጀመሪው መምጣቱ ወቅት የአዲስ ኪዳኑን ቃል ኪዳን ተስፋ ሙሉ በሙሉ ፈጽሞ ወደ ምድር እንዳላመጣው ማስታወስ ይገባናል፡፡ ስለዚህ፣ እርሱና የእርሱ ሐዋርያት እውነተኛ አማኞች ለእግዚአብሔር ታማኝ ሆነው መዝለቅ እንደሚገባቸው ያስጠነቅቃሉ ምክንያቱም ገና ሙሉ በሙሉ ወደ ፍፅምና ደረጃ አልደረስንምና ነው፡፡ ከዚያም ባሻገር ጳውሎስ በ2ኛ ቆሮንቶስ እና በገላትያ 2፡4 "ሐሰተኛ ወንድሞች" ብሎ የሚጠራቸው ገና በመካከላችን አሉ፡፡ በቃል ኪዳን ታማኝ ሆኖ ስለመዝለቅ የቀረበው ጥሪ አሁንም በሂደት ላይ ነው ምክንያቱም ይህ አዲስ ኪዳን በፍጹምነት ወደሙላት የሚመጣበትን ጊዜ እየተጠባበቅን ነውና፡፡

# እድገት

በበርካታ መንገዶች፣ ስለ መንግሥቱ አጀማመር የኢያሱን መጽሐፍ ክርስቲያናዊ ተዛምዶውን እንዳስተዋልን ሁሉ ስለ ክርስቶስ መንግሥት እድገትም አዲስ ኪዳን ከሚያስተምረው ጋር ተዛማጅነት ያለውን ነገር እናስተውላለን፡፡

**በድል አድራጊነት መውረስ**

አዲስ ኪዳን የክርስቶስን መንግሥት መስፋፋት/እድገት ሲገልጸው መንፈስ ቅዱስ በቤተክርስቲያን ውስጥ በሚሠራበት ወቅት የእርሱ በድል አድራጊነት የመውረሱ ሥራ በመላው ዓለም ላይ እየተስፋፋ የሚሄድበት ወቅት እንደሆነ ነው፡፡ በ1ኛ ቆሮንቶስ 15፡25 ጳውሎስ፣ "(ክርስቶስ) ጠላቶቹን ሁሉ ከእግሩ በታች እስኪያደርግ ድረስ ሊነግሥ (በሰማይ) ይገባዋልና።" እንዳለው ማለት ነው፡፡ ነገር ግን እንደ ቤተክርስቲያን የእኛ ተልዕኮ፣ ከኢየሱስ፣ ከሐዋርያቱና ከነቢያቱ የተለየ ሊሆንና ስጋዊ ሰይፍ ልናነሳ አይገባንም፡፡ ይልቁኑ፣ ኢየሱስ በመጀመሪያው መምጣቱ እንደመሠረተልን በዚው ባበለሁለት ዘርፍ ስልት ልንቀጥል ይገባናል፡፡

በአንድ በኩል፣ የሰይጣንንና የክፉ መናፍስቱን ሽንፈት በመላው ዓለም በማወጅ ድሉን ልናስፋፋ ይገባናል፡፡ ኤፌሶን 6፡12 እንደሚነግረን "መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለምና፥ ከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዦች ጋር በሰማያዊም ስፍራ ካለ ከክፋት መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር ነው እንጂ።" በሌላው ጎን ደግሞ፣ በዚህ ዘመን በዓለም ላይ እኛ ክርስቶስን በመወከል የምሥራቹን እያወጅን ስለሚመጣው የእግዚአብሔር ፍርድም ሰዎችን እያስጠነቀቅን የእግዚአብሔርን ምህረት ይቅርታና የዘላለም ሕይወት እናስተዋውቃለን፡፡ በ2ኛ ቆሮንቶስ 5፡20 ውስጥ፣ "እኛ የክርስቶስ

መልክተኞች (አምባሳደሮች) ነን፤ ከእግዚአብሔር ጋር ታረቁ ብለን ስለ ክርስቶስ እንለምናለን።” ተብሎ እንደተጻፈው ማለት ነው፡፡

## የነገዶች የርስት ክፍፍል

የእግዚአብሔር ህዝብ ዓለምን ሁሉ እንደሚወርስ የምንጠብቀው ጥበቃ በቤተክርስቲያን ዘመን ውስጥ የእርሱ መንግሥት ሲስፋፋ እያደገ እንደሚመጣም እናስተውላለን፡፡ ኢየሱስ ከእግዚአብሔር የተላከ ሁሉን ወራሽ የመሆኑን እውነታ ተረጋግጦ የምናየው በመላው ዓለም የሚኖሩ ሰዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ በሚጨምር መልኩ እርሱን የሕይወታቸው ጌታ ሲደርጉት ስናስተውል፤ ክርስቶስም የመንፈስ ቅዱስን ቀብዱ በመላው ዓለም በሚኖሩ ሰዎች ላይ በማፍሰስ ሥራውን እየቀጠለ መሆኑን ስናስተውል ነው፡፡ ገላትያ 3፡29፣ “እናንተም የክርስቶስ ከሆናችሁ እንኪያስ የአብርሃም ዘር እንደ ተስፋውም ቃል ወራሾች ናችሁ።” በማለት ይነግረናል፡፡ ሮሜ 8፡16-17 ደግሞ፣ “የእግዚአብሔር ልጆች .... ልጆች ከሆንን ወራሾች ደግሞ ነን፤ ... ከክርስቶስ ጋር አብረን ወራሾች ነን።” ይላል፡፡

### በቃል ኪዳን መታመን

በበርካታ መንገዶች፣ ኢያሱ በቃል ኪዳን ታማኝ ሆኖ ስለመዘለቅ የሰጠው አፅንዖት በክርስቶስ መንግሥት መስፋፋትም ውስጥ እውነት ሆኖ እንዴት እንደሚዘልቅ እናስተውላለን፡፡ ቤተክርስቲያን በዓለም ሁሉ እየሰፋች ስትሄድ፣ በአዲሱ ኪዳን የተገለጠው በደሙ የሆነው ስርየት ለመዳን የሚበቃ እምነት ያላቸውን ሁሉ እየሸፈነ ይሄዳል፡፡ በክርስቶስ ያመኑት ሁሉ ከዘላለማዊው ፍርድ ሙሉ በሙሉ ነፃ ይወጣሉ፡፡ ሆኖም ደግሞ በየዘመናቱ የምትመጣውም ቤተክርስቲያን በቃል ኪዳን ታማኝ ሆና እንድትዘልቅ ተጠርታለች፡፡

በአንድ ጎን፣ እውነተኛ አማኞች ለእግዚአብሔር ባላቸው መሰጠት እያደጉ መሄድ ይኖርባቸዋል፡፡ በዕብራውያን 12፡14፣ “...ሰላምን ተከታተሉ ትቀደሱም ዘንድ ፈልጉ... ያለ እርሱ ጌታን ሊያይ የሚችል የለምና።” የሚለውንና የመሳሰሉት ምንባቦች የሚሰጡትን ማስጠንቀቂያ ልብ ማለት ይገባቸዋል፡፡ በሌላ ጎን ደግሞ፣ በመካከላችን ያሉ ሐሰተኛ ወንድሞችም ማስጠንቀቂያ ሊሰጣቸውና ንስሓ በመግባት ሊድኑ ይገባቸዋል፡፡ ዕብራውያን 10፡26-27 እንደሚስቀምጠው፡ “የእውነትን እውቀት ከተቀበልን በኋላ ወደን ኃጢአት ብናደርግ ከእንግዲህ ወዲህ ስለ ኃጢአት መሥዋዕት አይቀርልንምና፥ የሚያስፈራ ግን የፍርድ መጠበቅ ተቃዋሚዎችንም ሊበላ ያለው የእሳት ብርታት አለ።”

> ***በቃል ኪዳን ታማኝ ሆኖ መዝለቅና ተሃድሶ የተሰኘው መሪ ሃሳብ በኢያሱ መጽሐፍ ውስጥ ከሚገኙ ወሳኝ ርዕሶች መካከል አንዱ ነው፡፡ በኢያሱ መጽሐፍ ውስጥ በምናገኘውና ኢያሱ ከሚመራው ከእያንዳንዱ ጦርነት በኋላ፣ ቃል ኪዳንን የማደስና በቃል ኪዳኑ አውድ መሰረት ለጌታ ታማኝ ሆኖ መዝለቅን የማደስ በዓል ይደረጋል፡፡ ይህ መሪ ሃሳብ ለእኛም እንደ ክርስቲያኖች ወሳኝ ነው ምክንያቱም እኛም ከጌታ ጋር ቃል ኪዳን ያለን ሰዎች ነንና፡፡ ያም ቃልኪዳን ክርስቶስ በደሙ ከእኛ ጋር ያደረገው አዲስ ኪዳን ነው፡፡ በቃል ኪዳን የመታመን መሪ ሃሳብ ጌታ ከአደረገው አንድ ነገር ጋር የተቆራኘ ነው ያም ከጌታ ደግነትና ከጌታ ጸጋ ጋር በእጅጉ የተያያዘ ነው፡፡ እንግዲያው፣ ጌታ ለእስራኤል መልካምነቱን በማሳየት ለእነርሱ የገባውን ቃል ኪዳን እንደፈጸመ ሁሉ፣ እነርሱም በቃል ኪዳኑ መሠረት ለጌታ ታማኝ ሆነው መዝለቅ እንደሚገባቸው ኢያሱ ለእስራኤላውያን ማሳሰቡ እጅግ ወሳኝ ነው ማለት ነው፡፡ ይኸው ተመሳሳይ ነገር ለእኛም ተግባራዊ ይሆናል፡፡ ጌታ በክርስቶስ አማካይነት መልካምነቱን አሳይቶናል፣ እኛም በጸጋው አማካይነት ድነትን ተቀብለናል፡፡ በውጤቱም፣ እኛም ለጌታ ታማኝ መሆን ይገባናል፣ ይህም የሚገለጠው በመታዘዛችን ማለትም የጌታን ትዕዛዛትና ህግጋት በመፈጸም ነው፡፡ የመታዘዝን፣ የታማኝነትንና የቃል ኪዳን አክባሪነትን ሕይወት ስንኖር፣ ገና ከጅማሬው አንስቶ ጌታ ለእኛ ስላደረገልን ነገር ያለንን ምሥጋና እንገልጣለን፡፡ በቃል ኪዳኑ አማካይነት በረከትንና ደግነትን ሊደርግልን የመጀመሪያውን እርምጃ የወሰደው ጌታ ራሱ ነው፣ ስለዚህ እኛም በዚያው የቃል ኪዳን አውድ መሠረት ለእነዚህ በረከቶችና ቸርነቶች አማካይነት ለጌታ የመታዘዝ ምላሻችንን መስጠት ይጠበቅብናል፡፡***
>
> ***ሬቨረንድ ሸሪፍ ጊንዲ፣ ትርጉም***

## ፍጻሜ

በኢያሱ መጽሐፍ ላይ የምናደርገው ክርስቲያናዊ ተዛምዶ በክርስቶስ መንግሥት አጀማመርና እድገት ውስጥ እንዴት እንደሚገለጥ ከተመለከትን፣ አሁን ደግሞ በጥቂቱ የመንግሥቱን ፍጻሜ ወደ መመልከቱ ዘወር ማለት ይገባናል፡፡ በክርስቶስ የወደፊት እና የፍጻሜ ሙላት ላይ ያለንን ተስፋ በኢያሱ መጽሐፍ በምናገኘው ብርሃን መሠረት እንዴት ልናዛምደው ይገባናል?

### በድል አድራጊነት መውረስ

የክርስቶስ መንግሥት ፍጻሜ ዓለምን በጠቅላላ በድል አድራጊነት የመውረሱ ማጠቃለያ እንደሚሆን አዲስ ኪዳን ያለምንም ጥያቄ ያመለክተናል፡፡ የሰይጣንንና የክፋት መናፍስቱን ሽንፈት ያጠናቅቀዋል፡፡ ኢየሱስ በድል ሲመለስ፣ እግዚአብሔር ላላመኑት የዘረጋው ምሕረት ያበቃል፡፡ ያን ጊዜ፣ በኢያሱ ዘመን እግዚአብሔር በከነዓናውያን ላይ ያመጣው ፍርድ ክርስቶስ የእግዚአብሔርን ፍርድ በጠላቶቹ ላይ ከሚመጣው ጋር ሲተያይ እጅግ አናሳ ሆኖ እናየዋለን፡፡ በራእይ 19፡14-15 ያለውን ስናነብብ፣ “በሰማይም ያሉት ጭፍራዎች ነጭና ጥሩ ቀጭን የተልባ እግር ልብስ ለብሰው በአምባላዮች ፈረሶች ተቀምጠው ይከተሉት ነበር አሕዛብንም ይመታበት ዘንድ ስለታም ሰይፍ ከአፉ ይወጣል፤ እርሱም በብረት በትር ይገዛቸዋል፤ እርሱም ሁሉን የሚገዛ የእግዚአብሔርን የብርቱ ቍጣውን ወይን መጥመቂያ ይረግጣል” ይላል፡፡

### የነገዶች ርስት ክፍፍል

በእርግጥም፣ ክርስቶስ በመንግሥቱ ፍጻሜ ወቅት ዳግመኛ ሲመለስ፣ ዓለምን የመውረሱ ነገር ማለትም ሁሉን ወራሽ መሆን መብቱ፣ ሙሉ በሙሉ ተፈጽሞ እናየዋለን፡፡ በራእይ 11፡15፣ “የዓለም መንግሥት ለጌታችንና ለእርሱ ለክርስቶስ ሆነች” ተብሎ እናነብባለን፡፡ ይህም የዓለም መንግሥት ክርስቶስን ለሚከተሉ ሁሉ ይሰጣል፡፡ ማቴዎስ 25፡34 እንደሚነግረን፣ አንድ ቀን በፍጻሜው የፍርድ እለት፣ “ንጉሥም በቀኙ ያሉትን እንዲህ ይላቸዋል፦ እናንተ የአባቴ ቡሩካን፥ ኑ፤ ዓለም ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ውረሱ።” ይላቸዋል፡፡

### በቃል ኪዳን መታመን

የእግዚአብሔር ህዝብ ለቃል ኪዳን ታማኝ ሆኖ እንዲዘልቅ የተሰጠው ማስጠንቀቂያ የሚያበቃው በክርስቶስ መንግሥት ፍጻሜ ላይ ብቻ ነው፡፡ ክርስቶስ ሲመለስ፣ በሚያድን እምነት ወደ እርሱ ያልመጡ ሁሉ በእግዚአብሔር ዘላለማዊ ፍርድ ስር ይወድቃሉ፡፡ እውነተኛ አማኝ የሆኑት ሁሉ ደግሞ ወደ አዲሲቷ ምድር ይገባሉ በዚያም የአዲሱን ኪዳን በረከቶች በሙላት ይቀበላሉ፡፡ ራእይ 22፡3 እንደሚነግረን፣ “ከእንግዲህም ወዲህ መርገም ከቶ አይሆንም። የእግዚአብሔርና የበጉም ዙፋን በእርስዋ ውስጥ ይሆናል፥ ባሪያዎቹም ያመልኩታል፥ ፊቱንም ያያሉ፥”

በፍጻሜውም፣ ክርስቶስ በመንግሥቱ አጀማመር፣ እድገትና ፍጻሜ አማካይነት በኢያሱ መጽሀፍ የተጠቀሱትን መሪ ሃሳቦች እንዴት ወደ ፍጻሜ እንዳመጣቸው እንድናስታውስ አዲስ ኪዳን ያሳስበናል፡፡ ያንንም ስናደርግ፣ በኢያሱ ዘመን ተከናውነው የነበሩት የእስራኤል በድል መውረስ፣ የርስት ክፍፍልና በቃል ኪዳን መታመን፣ ክርስቶስ በመጀመሪያው መምጣቱ ምን እንዳከናወነ ከመረዳት አንጻር ያለንን ግንዛቤ በእጅጉ ያሳድግልናል፡፡ በዕለት ከእለት ሕይወታችን እንዴት እግዚአብሔርን በማገልገል መመላለስ እንደሚገባን ያስተምሩናል፡፡ ደግሞም፣ ድሉ ሲጠናቀቅ፣ የአዲሱ ፍጥረት ውርሶች የእኛ ሲሆኑ፣ እኛም በክርስቶስ የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ንጉሣዊ ህዝቦች መሆናችን ሲረጋገጥ ወደሚከናወነው ዐቢይ የታሪክ ፍጻሜ ያመለክቱናል፡፡

# ማጠቃለያ

“የመጽሐፈ ኢያሱ መግቢያ” በተሰኘው ትምህርታችን ሦስት ወሳኝ ጉዳዮችን አንስተናል፡፡ በመጀመሪያ፣ የመጽሐፉን ጸሐፊና ዝመኑን የዳሰስን ሲሆን፣ ያንንም ስናደርግ በጉዳዩ ላይ ትውፊታዊውን፣ ነቀፋ ፈላጊውንና የወንጌል አማኞችን አመለካከቶች ለማካተት ሞክረናል፡፡ ሁለተኛ፣ የኢያሱን ንድፍና ዓላማ የመጽሐፉን ይዘትና አወቃቀር ደግሞም ቀደምት ትርጓሜውንም ከግምት ውስጥ በማስገባት መርምረናል፡፡ ሦስተኛ ደግሞ፣ ክርስቶስ በእግዚአብሔር የከበረ መንግሥት አጀማመር፣ እድገትና ፍጻሜ አማካይነት በኢያሱ መጽሐፍ ሙላታቸው በጉጉት ሲጠበቅ የነበሩትን ሁሉ እንዴት እንደፈጸማቸው በመመርመር ከኢያሱ መጽሐፍ ያገኘናቸውን ሃሳቦች ክርስቲያናዊ ተዛምዶዎችም ዳሰሰናል፡፡

መጽሐፈ ኢያሱ በኢያሱ ሕይወት አማካይነት እግዚአብሔር ምን ምን ነገሮችን እንዳከናወነላቸው በማሳየት በዘመናቸው ችግሮችን በሚጋፈጡበት ጊዜ የተደረገላቸውን በማሰብ እንዲጸኑ የጥንት እስራኤላውያንን ያሳስባል፡፡ በበርካታ መንገዶችም፣ እኛም በዚህ ዘመን ከብዙ ፈተናዎች ጋር እንጋፈጣለን፡፡ በዚህ ተከታታይ ትምህርት እንደምንመለከተው፣ እግዚአብሔር በእነርሱ ዘመን ለሚሠራው ሥራ የሚኖራቸውን ግለት ለማደስ የሚያስችሏቸውን ዕድሎች መጽሐፈ ኢያሱ ለእስራኤላውያን ያሳያቸዋል፡፡ እኔና እናንተም ለተሃድሶ የሚጠቅሙ እድሎችን እንድናስተውል መጽሐፉ ያግዘናል፡፡ ስለዚህ መጽሐፍ ይበልጥ ስንረዳ፣ በብሉይ ኪዳን ዘመን እግዚአብሔር በኢያሱ አማካይነት ስለ ሠራቸው ሥራዎች በሚኖረን እውቀት በማደግ ብቻ አናቆምም፣ ይልቁኑ እግዚአብሔር በታላቁ ኢሱ፣ በአዳኛችን በኢየሱስ አማካይነት አስቀድሞ ስላከናወናቸው፣ እያከናወናቸው ስላሉትና ወደፊትም ገና ስለሚከናውናቸው ነገሮችም ጭምር ጠንቅቀን በማወቅም ጭምር እናድጋለን፡፡